# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ማክሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 022 መስከረም 22 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# ‹‹የተፈጥሮ ሀብቶቻችንን በአግባቡ በመጠበቅ ለትውልድ የሚሻገር ሥራ መሥራት ያስፈልጋል››

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አዲስ አበባ፡- በየአካባቢው ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ በማወቅ፣ በመጠቀምና በመጠበቅ ለትውልድ የሚሻገር ሥራ መሥራት እንደሚገባ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በቤንቺ ሼኮ ዞን የነበራቸውን የመስክ ጉብኝት አስመልክተው ትናንት በሰጡት ማብራሪያ እንዳሉት፤ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ስንሄድ ያልተነኩ እምቅ ሀብቶች ይገኛሉ። እነዚህን ሀብቶች በአግባቡ ማወቅ፣ መጠበቅና ሀብቶቹን በመጠቀም ለትውልድ የሚሻገር ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።

10 ሄክታር የሚደርስ ቡና የተተከለበትን በበቃ በማሳያነት ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከጥቂት ዓመታት በፊት ከአንድ ኩንታል ያልበለጠ ምርት ይገኝበት ነበር። አሁን ላይ በተሠራ የምርጥ ዘር ማሻሻያ ከሄክታር እስከ 10 ኩንታል ቡና እየተገኘበት ነው። አንዳንድ ቦታዎች ላይም በሄክታር እስከ 20 ኩንታል ድረስ ማግኘት ተችሏል ብለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ በዞኑ ማር፣ ቁንዶ በርበሬ፣ እርድ፣ የጎማ ዛፍ እና ወርቅን ጨምሮ ሌሎችም እምቅ ሀብቶች እንደሚገኙ ጠቅሰው፤ አካባቢውን ለኢንቨስትመንትና ለቱሪዝም በማዋል የሕዝቡን የኑሮ ዘዬ መቀየርና ማሻሻል እንደሚቻል ገልጸዋል።

ዓይናችንን ገልጠን ያለንን ሀብት ካላየን ልንጠቀምበት አንችልም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ሀገሩን ያላወቀና ሀብቱን በአግባቡ ያልተጠቀመ ደግሞ የባከነ ይሆናል። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን አቅማችንን አስተባብረን ሀገራችንን ለማወቅ፣ በየአካባቢያችን ያሉ ፀጋዎችን ለመገንዘብና በአግባቡ ለመጠቀም ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅብናል ብለዋል።

ያለንን እውቀት፣ ሀብትና ጊዜ ጥቅም ላይ በማዋል ብልጽግናችንን ለማረጋገጥ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መኖሩን መገንዘብና የአመለካከት ለውጥ ማምጣት እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤ በየአካባቢው ያለውን እምቅ አቅም የተረዳ ዜጋ


«የተፈጥሮ ሀብቶቻችንን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# በሰው ዘር መገኛዋ ‘ሰው’ ሆኖ የተገኘው መምህር

**ዳግማዊት ግርማ**

አንዋር መሐመድ ይባላል። ከወዳጆቹ ተግባቢ ነው። እያስተማረ ይማራል። በተማሪዎቹም ይወደዳል። ከእናቱ ማኅፀን ከወጣ 36 ዓመታት ሆኖታል። በመምህርነት ሳለ 16 መስከረሞች አልፈዋል። የንግድ አስተዳደር የድህረ ምረቃ ትምህርቱን ይማራል። በ11ኛው የበጎ ሰው ሽልማትም በመምህርነት ዘርፍ ታጭቷል።

በደሴ መምህራን ማሠልጠኛ በመምህርነት ዲፕሎማ አለው። ከወሎ ዩኒቨርሲቲ በጂኦግራፊ የመጀመሪያ ዲግሪ ይዟል። በትምህርት አመራር የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ አግኝቷል። ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ በርዕሰ መምህርነት እያገለገለ ይገኛል፤ በመሐመድ ሁመድ አጠቃላይ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት። ትምህርት ቤቱ ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ እስከ ስምንተኛ ድረስ ያስተምራል።

መምህር አንዋር ምድርን የተቀላቀለው በአሰብ ነው። ወሎ ደሴ ላይ አድጓል። አፋር ተድሮ ልጅ ያፈራበት ነውና


በሰው ዘር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




አቶ አንዋር መሐመድ

# «ኢሬቻ ማኅበራዊ ትስስርና አንድነትን በመፍጠር ለኢኮኖሚ ግንባታ ያለው ፋይዳ የጎላ ነው»

- አቶ ቀጄላ መርዳሳ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ኢሬቻ በሕዝቦች መካከል ማኅበራዊ ትስስርና አንድነትን በመፍጠር ለኢኮኖሚ ግንባታ ያለው ፋይዳ የጎላ መሆኑን የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ ገለጹ፡፡

34ኛው የጉሚ በለል የውይይት መድረክ «ኢሬቻ፤ የአንድነትና የወንድማማችነት አርማ» በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት ተካሂዷል፡፡

በመርሐግብሩ የተገኙት የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ እንደገለጹት፤ ኢሬቻ በቱሪዝም ዘርፍ


«ኢሬቻ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ አዮብ ተፈሪ

# አማራ ክልል ከቱሪዝም ዘርፍ 7 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ለማግኘት አቅዷል


ገጽ 4










# በአፍሪካ
## የመጀመሪያ የሆነ ዓለምአቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ በአዲስ አበባ ሊካሄድ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነው «ውሜን ኢን ኮፊ» ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ እ.ኤ.አ በመጪው ጥቅምት 16 እስከ 22 በአዲስ አበባ ሊካሄድ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣንና ውመን ኢን ኮፊ ኢትዮጵያ ከትናንት በስቲያ በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ እኤአ በመጪው ጥቅምት 16 እስከ 22 የመጀመሪያ የሆነው ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ በአዲስ አበባ ሊካሄድ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

የውሜን ኢን ኮፊ ኢትዮጵያ ቦርድ ሰብሳቢ ወይዘሮ ሳራ ይርጋ መግለጫውን በሰጡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ የቡና ኤግዚቢሽኑና ኮንፍረንሱ የኢትዮጵያን ቡና ለማስተዋወቅና የገበያ ትስስር ለመፍጠር ያግዛል፡፡

ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽኑና ኮንፍረንሱ የኢትዮጵያን ቡና ከማስተዋወቁም ጎን ለጎን ኤክስፖርት በሚደረግበት ጊዜ ለትራንስፖርትና ለሆቴሎች የሚወጡ ወጪዎችን ለመቀነስ እንደሚረዳም ነው ወይዘሮ ሳራ ያነሱት፡፡

እንደ ወይዘሮ ሳራ ገለጻ፤ በኮንፍረንሱ የ33 ሀገራት ውሜን ኢን ኮፊ ኃላፊዎች፣ ምሁራን፣ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅራቢዎችና የዘርፉ ባለሙያዎች ይሳተፋሉ፡፡

በኮንፍረንሱ ሀገሪቱ የቡና መገኛ ብቻ ሳትሆን የቡና ቱሪዝም መዳረሻ ጭምር መሆኗን የሚያሳይ በቂ ዝግጅት አድርገናል ያሉት የቦርድ ሰብሳቢዋ፤ ባህላዊ የቡና አፈላል ሥነሥርዓትን ለጎብኚዎች የማስተዋወቅ እንዲሁም ከማምረት እስከ መቅመስ ድረስ ያለውን ሂደት እንዲመለከቱ ይደረጋል ብለዋል፡፡

የቦርድ ሰብሳቢዋ አክለውም፤ ኮንፍረንሱ ቡና በሚደርስበት ወቅት ላይ መካሄዱ የኢትዮጵያ ቡናን ይበልጥ ለማስተዋወቅ እንደሚረዳ ጠቁመዋል፡፡

በኮንፍረንሱ ዘርፉን የሚያነቃቁ ጥናታዊ ጽሑፎችና የአንድ ቀን የቡና ኤክስፖ ይቀርባል ያሉት ወይዘሮ ሳራ፤ ከ250 እስከ 300 የሚደርሱ የተለያዩ ሀገራት ዜጎች እንደሚሳተፉም ነው የተናገሩት፡፡

እንደ ወይዘሮ ሳራ ገለጻ፤ ተሳታፊዎቹ አራት ዋና ዋና የቡና መብቀያ ቦታዎች ላይ የመስክ ጉብኝት እንዲያደርጉ ይደረጋል ያሉ ሲሆን፤ ሲዳማ፣ ከፋ፣ ይርጋጨፌ የመስክ ምልከታ ከሚደረግባቸው ቦታዎች መካከል ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መሐመድ ሽምሱ በበኩላቸው፤ ኮንፍረንሱ የኢትዮጵያን ቡና ተፈላጊነትና የገበያ መዳረሻ ለማስፋት እንዲያስችል በቂ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል፡፡

ከቡና አቅርቦት ጥራት አኳያ በሆቴሎች የሚቀርብ የተፈላ ቡና ጥራት ያለው እንዲሆን ከሆቴሎች ጋር እየሠራን እንገኛለን ያሉት አቶ መሐመድ፤ በኮንፍረንሱ በዘርፉ ያሉ በርካታ ችግሮች የሚቀረፉበት ጥናታዊ ጽሑፎች እንደሚቀርቡ ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ መሐመድ ገለጻ፤ ኮንፍረንሱ የኢትዮጵያን ቡና ተፈላጊና የገበያ መዳረሻ ለማሳደግ ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡

በኮንፍረንሱ እስከ 50 የሚደርሱ ሀገራት የሚሳተፉ ሲሆን፤ የሀገሪቱን የቡና ቱሪዝም ለማነቃቃትም የመስክ ምልከታ ተደርጎ የልምድ ልውውጥ እንደሚደረግ በመግለጫው ተመላክቷል፡፡

# ከስልጤ ዞን የቱሪስት መስህቦች ተጠቃሚ ለመሆን ከቁጭት በመውጣት መሥራት ይገባል

**ኃይሉ ሣህለድንግል**


ወራቤ፡- የስልጤ ዞን የቱሪስት መስህቦችን በማልማት፣ በማስተዋወቅና ለገበያ በማቅረብ ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን ከቁጭት ወጥቶ ተግባራዊ ሥራ ውስጥ መግባት እንደሚገባ ተገለጸ፡፡

የዓለም ቱሪዝም ቀን በዓለም ለ44ኛ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ36ኛ ጊዜ ‹‹አረንጓዴ ልማት ለቱሪዝም፣ ቱሪዝም ለአረንጓዴ ልማት›› በሚል መሪ ሃሳብ በስልጤ ዞን ወራቤ ከተማ ከትናንት በስቲያ በተከበረበት ወቅት እንደተጠቆመው፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በስልጤ ዞን በርካታ የተፈጥሮ፣ ባህላዊ፣ ሰው ሠራሽና ሃይማኖታዊ የቱሪዝም እምቅ ሀብቶች ቢኖሩም፣ ከእነዚህ ሀብቶች ተጠቃሚ መሆን አልተቻለም፡፡ ዞኑ የቱሪስቶች መተላለፊያ እንጂ በቱሪስቶች የሚጎበኝ መዳረሻ ሳይሆን ቆይቷል፡፡

በበዓሉ አከባበር ላይ የተገኙት የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ንጉሡ ጥላሁን የስልጤ ዞን አያሌ የቱሪስት መዳረሻዎች እንዳሉት በመድረኩ ከቀረቡ ዝግጅቶች መረዳታቸውን አስታውቀዋል፡፡ ዞኑ ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ለኢኮኖሚ እድገት፣ የኅብረተሰቡን ሕይወት ለመቀየር፣ አካባቢውን ከሌሎች አካባቢዎች ለማስተሳሰር፣ ባህሉን እንዲያስተዋውቅ፣ አካባቢውም የሌሎችን ባህል እንዲያውቅ በአጠቃላይ በሀገሪቱም፣ በቀጣናውም፣ በዓለምም ደረጃ እንዲታወቅ የሚያደርጉ እጹብ ድንቅ የቱሪስት መስህቦች እንዳሉት መገንዘባቸውን አስታውቀዋል፡፡

መስህቦቹ ለዞኑም ለሀገርም ጠቀሜታ ሳይሰጡ በመኖራቸው ቁጭት መፈጠሩንም ጠቅሰው፣ ቁጭቱን ወደ ተግባር በመቀየር ከዘርፉ ለመጠቀም መረባረብ እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡ ከመስህቦቹ ተጠቃሚ ለመሆን አሁን መሥራት መጀመራችን ትክክለኛ ወቅት ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ በእዚህ ጉዳይ ላይ እየተነጋገርን ያለነው የዓለም የቱሪዝም ቀን እየተከበረ ባለበት፣ የዞኑን የቱሪስት መስህቦች ለማልማት፣ ለማስተዋወቅና ለገበያ ለማቅረብ ወሳኝ ሚና ያላቸውና በቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት የተደረጉ የጥናት ሰነዶች ለርክክብ በቀረበበት ወቅት መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

የተጀመረውን የጥናት፣ ምርምርና ሥልጠና የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትን፣ የወራቤ ዩኒቨርሲቲን እንዲሁም ወራቤ ያለውን የቴክኒክና ሙያ ተቋም ይዘን አብረን እንሠራለን ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ከችግሮቹ አንድ ሁለቱ በኢንስቲትዩቱ ጥናት መፈታታቸውንም ጠቅሰዋል፡፡ ኢንስቲትዩቱ የቱሪስት ካርታ መሥራቱን የስልጤ ማኅበረሰብ ባህላዊ ምግቦች አዘገጃጀትን መሰነዱን ጠቁመው፤ አሁን በተከናወነው ተግባር አንድ እርምጃ ወደፊት መሄድ እንደተቻለም አስታውቀዋል፡፡



አተካኖ ከስልጤ ባህላዊ ምግቦች አንዱ ነው

የስልጤ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ዓሊ ከድር የዞኑን የቱሪዝም ሀብቶች በመጠበቅ፣ በማልማትና በማስተዋወቅ በኩል ባለፉት አመታት የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት በማቋቋም እምቅ አቅሞችንና ተግዳሮትን ለመለየት ጥናቶች ተደርገው ወደ ሥራ የተገባ መሆኑን ጠቅሰው፣ ቱሪዝም ለገበያ እንዲውል ከማድረግ አኳያ አሁንም ችግሮች እንደሚስተዋሉ አመልክተዋል፡፡

ዋና አስተዳዳሪው የዞኑ አስተዳደር ችግሮቹን ለመፍታት የጀመራቸውን ሥራዎች አጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፣ ያሉትን ሀብቶች በመጠበቅና በመንከባከብ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚያስችሉ ጥናቶችና ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ ብለዋል፡፡

በመዳረሻ ልማት፣ ገበያና ፕሮሞሽን፣ በቱሪዝም ምርት አገልግሎቶች ጥራት ላይ ያተኮሩ ተግባሮች በስፋት እንደሚከናወኑ አስታውቀው፣ የግል ባለሀብቶችም የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በብዛትና በጥራት በመገንባት ችግሩን ለመፍታት እንዲረባረቡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ዞኑ ከአዲስ አበባ ቅርብ ርቀት ላይ እንዲሁም በደቡብ የቱሪዝም ኮርደር ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው፣ እነዚህ ተግባሮች ከተከናወኑ የቱሪዝም ሀብቶችን በቀላሉ ለገበያ ማቅረብ ይቻላል የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ ሁላችንም እጅ ለእጅ ተያይዘን በአካባቢያችን ያሉትን ጸጋዎች ለመሸጥ በተቀናጀ መንገድ በመሥራት የስልጤ ማኅበረሰብን ከፍ እናድርግ፣ የስልጤ ማኅበረሰብ ከፍ ሲል ኢትዮጵያም ከፍ ትላለች፤ ሁላችንም በዚህ ሥራ ላይ እንረባረብ ብለዋል፡፡

የዞኑ የቱሪስት ዘርፍ ማነቆ ከሆኑት መካከል የቱሪስት ጋይድ ማጥና የቱር ፓኬጅ አለመኖር መሠረታዊ ችግሮች እንደነበሩ አስታውሰው፣ ይህን ችግር የቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ጥናት አድርጎ ሰነድ ማዘጋጀቱን አስታውቀዋል፡፡ በስልጤ ባህል ምግቦች ላይም ተመሳሳይ ጥናት አድርጎ ማንዋል በማዘጋጀት ባህላዊ ምግቦቹ የእሴት ሰንሰለቱን ጠብቀው እንዴት እንደሚዘጋጁ የሚሳይ የጥናት ሰነድ ማዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

የዓለም ቱሪዝም ቀን መስከረም 19 እና 20 ቀን 2016 ዓ.ም በስልጤ ዞን ወራቤ ከተማ በፓናል ውይይትና ከዞኑ የመስህብ ስፍራዎች አንዱ በሆነው የሀረ ሼጣን ሐይቅ ጉብኝት በማድረግ ተከብሯል፡፡ የስልጤ ብሔረሰብ ባህላዊ ምግቦች አዘገጃጀታቸውን የሚያስቃኝ ዝግጅትም ለእይታ ቀርቧል፡፡ የቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ያዘጋጃቸውን ሰነዶችም ለዞኑ አስተዳደር አስረክቧል፡፡ በዓሉን ያዘጋጁት የቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት፣ የወራቤ ዩኒቨርሲቲና የስልጤ ዞን አስተዳደር ናቸው፡፡

# በወሊሶ ከተማ በ81 ሚሊዮን ብር የተለያዩ መሠረተ ልማቶች እየተገነቡ ነው

**ጌትነት ተስፋማርያም**



አዲስ አበባ፡ በ81 ሚሊዮን ብር ወጪ የኅብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ የተለያዩ መሠረተ ልማቶች እየተገነቡ መሆኑን የወሊሶ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ፡፡

በወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የመሠረተ ልማት የሥራ ሒደት መሪ አቶ ይርጋለም ፀጋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከኅብረተሰቡ ጋር በተደረጉ ውይይቶች መነሻ የሆኑ የመሠረተ ልማት ጥያቄዎችን ለመመለስ በ81 ሚሊዮን ብር የተለያዩ ግንባታዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡

ከመሠረተ ልማት ግንባታዎች መካከል የመዝናኛ ፓርክ፣ የመንገድና ድልድይ ግንባታ፣ የግብርና ክላስተር ሼዶች፣ የትምህርት ቤቶች ዕድሳት፣ የውሃ ማስወገጃ ቦይ ግንባታዎች ዋነኞቹ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

በ2016 በጀት ዓ.ም በአምቦ ዩኒቨርሲቲ ወሊሶ ካምፓስ አጠገብ በሚገኝ አካባቢ ትልቅ መዝናኛ ፓርክ ለመገንባት 11 ሚሊዮን ብር መመደቡን አስታውቀዋል፡፡

በከተማዋ ያለውን የመንገድ ሽፋን ለማሳደግ በ11 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር የጌጠኛ ድንጋይ መንገድ ንጣፍ ሥራ ይከናወናል ያሉት አቶ ይርጋለም፤ በኅብረተሰቡ ጥያቄ መሠረት በከተማዋ የሚገነባ ሰፊ ድልድይ እንዳለም ጠቁመዋል፡፡

የጎርፍ ውሃን አደጋ እንዳያደርስ ለመከላከልና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓቱን ለማዘመን የሚረዳ የውሃ ቦይ መስመር ግንባታ በ11 ሚሊዮን ብር እየተከናወነ መሆኑንም አስረድተዋል፡፡

ለተለያዩ የከተማዋ ነዋሪዎች የሚገነቡ የግብርና ክላስተር ሼዶች በእንስሳት ሀብት እርባታ፣ በዶሮና በተለያዩ የግብርና ውጤቶች ዘርፍ ለበርካታ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችሉ መሆናቸውንም አመላክተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ቀድሞ የተጀመረውን የከተማዋን የፍትሕ ቢሮ ሕንፃ ለማጠናቀቅ የሚያስችል ሥራ እንደሚከናወን አቶ ይርጋለም ተናግረዋል፡፡

የመሠረተ ልማቶቹ ግንባታ የከተማ ነዋሪውን ፍላጎት መሠረት ያደረጉና የወሊሶን ዕድገት ለማፋጠን እንደሚያግዙ ገልጸዋል፡፡

የመሠረተ ልማት ግንባታዎቹን በታቀደላቸው ጊዜና በጀት አጠናቆ ለአገልግሎት ለማብቃት አስፈላጊው የክትትል ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የፕሮጀክቶቹ ግንባታ ለነዋሪዎቹ ምቹ አገልግሎት ከማቅረብ በተጨማሪ ከተማዋን የቱሪዝም ማዕከል እንድትሆን የሚደረገውን ጥረት ያግዛል ብለዋል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት በከተማዋ የመንገድ ዳር መብራት፣ የአረንጓዴ ልማትና የተለያዩ የውበትና ቱሪዝም ሥራዎች መከናወናቸውን አስታውሰው፤ በአምስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር የገበያ ማዕከል ግንባታ መከናወኑንም አመላክተዋል፡፡

ባለፈው ዓመት የከተማዋን ልማትና ዕድገት በማፋጠን ረገድ ጉልህ ድርሻ ያላቸው የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች የተገነቡት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም ባቀረበው የገንዘብ ድጋፍ ነበር ያሉት አቶ ይርጋለም፤ በ2015 የከተማዋ በጀት 120 ሚሊዮን ብር እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

አሁን ላይ የፕሮጀክቱ ጊዜ በማለቁ የ2016 በጀት ዓመት ሙሉ በሙሉ በከተማ አስተዳደሩ የሚሸፈን ሲሆን፣ ለዓመቱ የተያዘውን የ81 ሚሊዮን ብር የልማት በጀት ከግብር፣ ከማዘጋጃ ቤታዊ ገቢና ከተለያዩ ምንጮች የሚሰባሰብ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡



ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ

# በኦሮሚያ ክልል መሠረታዊ የልማት ግቦችን ለማሳካት እየተሠራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል መሠረታዊ የልማት ግቦችን ለማሳካት እየተሠራ መሆኑን ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው፣ ርዕሰ መስተዳድር ሽመልስ አብዲሳ እና የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ለሁለት ቀናት በጅማ እና አካባቢው ያሉ የልማት ሥራዎችን ጎብኝተዋል፡፡

በጉብኝቱ የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ እንደተናገሩት፤ በክልሉ መሠረታዊ የልማት ግቦችን ለማሳካት እየተሠራ ነው። እነዚህም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት እና ወደ ውጭ የሚላክን ምርት ማሳደግ ናቸው።

ከዚህ አኳያ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተቀመጡ «ኢንሼቲቮችን» መነሻ በማድረግ በክልሉ በርካታ የልማት ሥራዎች መከናወናቸውን የተናገሩት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ለአብነትም በክልሉ በመኸር እና መስኖ የሚለማውን የመሬት ሽፋን በማሳደግ ረገድ ውጤታማ ሥራ መከናወኑን ጠቁመዋል፡፡

የልማት ሥራዎቹ በዋናነት የሕዝብ ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረጉ ናቸው ያሉት አቶ ሽመልስ፤ ከአማራ ክልል ተሞክሮ በመውሰድ ከሦስት ዓመት በፊት የተጀመረው የሩዝ ምርትም ውጤት እየተመዘገበበት መሆኑን ገልጸው፤ ይህም በሀገር አቀፍ ደረጃ በሩዝ ምርት ራስን ከመቻል ባለፈ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የተጀመረውን ሥራ ያጠናክራል ብለዋል።

እንደ ርዕሰ መስተዳድሩ ገለፃ፤ ባለፉት አምስት ዓመታት ያረጁ የቡና ዛፎችን በአዲስ በመተካትና በአዲስ መልክ የቡና ችግኞችን በመትከል በዘርፉ አበረታች ሥራ ተከናውኗል። በዚህም ከአምሥት ቢሊዮን በላይ የቡና ችግኞችን መትከል ተችሏል። አርሶ አደሩ የቡና ምርትን በቀጥታ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆን እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

በመኸርና በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በተሠሩ ሥራዎች ከፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያ ማቅረብ መቻሉን ጠቅሰው፤ በዚህም ኢትዮጵያ ለስንዴ ግዥ ታወጣው የነበረውን የውጭ ምንዛሬ ከማስቀረት ባለፈ ተጨማሪ ምንዛሪ ማስገኘት ተችሏል ብለዋል።

«በክልሉ ከፍተኛ የመልማት አቅም አለ። ይህንን አቅም በቴክኖሎጂ በማገዝ የበለጠ ውጤት ለማስመዝገብ እየተሠራ ነው» ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ይህን የአርሶ አደሩ ትጋት በአግባቡ መደገፍ እና ጠንክሮ መሥራት ከተቻለ በአጭር ጊዜ የላቀ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ተናግረዋል።

በኦሮሚያ ክልል የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማዕከል በማድረግ እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሥራዎች አበረታች ውጤት እያስመዘገቡ ነው። በቀጣይም የምርት ጥራት ላይ ትኩረት በማድረግ የወጪ ንግድን ለማሳደግ ጠንካራ ሥራዎች እንደሚሠሩም ገልጸዋል።

ጉብኝቱ በዋናነት በጅማ ዞን የተመዘገበው ስኬት፣ በአካባቢው የሚከናወኑ የሌማት ትሩፋት፣ የግብርና ሥራዎችን እና በቀጣይ ሊሠሩ የሚችሉ ሥራዎችን ለመለየት የተከናወነ ነው ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

# ሰውሠራሽና እምቅ የተፈጥሮ አቅሞችን በማጎልበት ረገድ ከባለሀብቶች ብዙ ይጠበቃል

**ግርማቸው ጋሻው**

ዳውሮ፡- እምቅ የተፈጥሮ አቅሞችን በማልማትና የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማሳደግ በሚደረገው ርብርብ ውስጥ ባለሀብቶች ጉልህ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ ቀረበ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሰላማዊት ካሳ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ የቱሪዝም አቅሞች አላት። መንግሥት በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተነሳሽነቱን በመውሰድ የገበታ ለሀገር፣ ገበታ ለሸገር እና ገበታ ለትውልድ በሚሉ መሪ ቃሎች የተለያዩ አካባቢዎችን ማልማት ተችሏል፡፡



የጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ

ባለፉት ሁለት ሳምንታት የቱሪዝም መዳረሻ ልማት ባለባቸው ቦታዎች ላይ የጋዜጠኞች ቡድን እየተዘዋወረ የተመለከተውም ይህን ነው ሲሉ ሚኒስትር ዴኤታዋ ተናግረዋል፡፡

«እንደ ሀላላ ኬላ ሪዞርትና ሌሎች መሰል የቱሪዝም መሠረተ ልማቶች እየተገነቡ ያሉት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተነሳሽነት መሆኑን የተናገሩት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ እሳቸው በቦታው ያለውን እምቅ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መስህቦች እንዲሁም በዚህ አካባቢ በተገነባው የጊቤ ሦስት ግድብ ምክንያት የተፈጠረው ሐይቅ ሌላ መስህብ እንደሚሆን በማየታቸው እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

እነዚያን ዓይነት እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶች ቀደም ሲል ተረስተው መቆየታቸውን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ነገር ግን ለአካባቢው ትኩረት በመሰጠቱ አሁን የምናየው አስደናቂ አካባቢ ተፈጥራል ብለዋል።

በጨበራ ጩርጩራ ፓርክ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ዓይነትና ብዛት አስደናቂ ነው ሲሉ የገለፁት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በተለይ በርካታ የዱር እንስሳት መኖራቸው ለዘርፉ ትልቅ አቅም መሆኑን ጠቅሰው፤ ለአብነትም በፓርኩ ወደ 1000 የሚጠጉ የአፍሪካ ዝሆኖች አሉ ብለዋል።

በፓርኩ ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ተስማምተው እንደሚኖሩ ለማየት ይቻላል ያሉት ወይዘሮ ሰላማዊት፤ በዙሪያው ያሉ ሰዎች እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅ አስተዋፅኦ ያደረጉ በመሆኑ ከተፈጥሮ ጋር ጠንካራ ትስስር አላቸው ብለዋል።

«አካባቢውን ከንግድና ኢንቨስትመንት አንፃር ስንመለከተው እዚህም እዚያም በቀላሉ የሚገኙ የብረት፣ የድንጋይ ከሰል፣ የወርቅ እንዲሁም በርካታ የማዕድናት ክምችት አለ። በቦታው ለቱሪዝም ብቻ ሳይሆን በቢዝነስ ረገድም ለሀገራችን ዕድገት የሚጠቅም ሰፊ አቅም አለ። ይህንን በመጠቀም መንግሥትም ሆነ የግል እና ዓለምአቀፍ ባለሀብቶች ወደዚህ በመምጣት ኢንቨስት እንዲያደርጉ የመንገድ፣ የመብራት እና የስልክ መሠረተ ልማት ዝርጋታ አከናውኗል፤ እየተከናወነም ይገኛል» ብለዋል።

ኅብረተሰቡ እንግዳ ተቀባይ መሆኑን ያወሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ይህ ባለሀብቶች ወደ ስፍራው ገብተው እንዲያለሙ አንዱ አስቻይ ሁኔታ መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡


ቱሪስቶችም ወደዚህ ስፍራ መጥተው በኅብረተሰቡ ተጠብቆ የቆየውን የሺህ አመታት ታሪክ እና የማኅበረሰብ እውቀት ሊካፈሉ ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# በደም እጦት ሕይወታቸውን የሚያጡ ሰዎችን ለማዳን ኅብረተሰቡ እንዲተባበር ጥሪ ቀረበ

**ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በደም እጦት ምክንያት ሕይወታቸውን የሚያጡ ሰዎችን ለማዳን ኅብረተሰቡ በደም ልገሳ ተግባር ላይ ሊሳተፍ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ፡፡ የከተማዋን ገፅታ በመገንባት የቱሪዝም ፍሰቱን ለማሳለጥ እየተሠራ እንደሚገኝም ተጠቅሷል፡፡





በኢትዮጵያ ለ36ኛ ጊዜ፣ በዓለም አቀፍ ደግሞ ለ44ኛ ጊዜ እየተከበር የሚገኘውን የዓለም የቱሪዝም ቀን በማስመልከት ቢሮው የደም ልገሳ መርሐ ግብር አከናውኗል፡፡

በሥነሥርዓቱ ላይ የአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ዘርፍ ም/ኃላፊ አቶ ሀፍታይ ገብረእግዚአብሔር እንደገለጹት፤ ሕይወትን ማዳን የሚጀመረው በአንድ ጠብታ ደም ነው፤ ደም በመለገስ በራሳቸው አቅም ታክምው መዳን የማይችሉ ሰዎችን በቀላሉ ለማዳን ያስችላል፤ ይህም ለሀገር ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ አበርክቶ ይኖረዋል፡፡

አቶ ሀፍታይ እንደገለጹት፤ ደም መለገስ በቀላሉ መዳን የሚችሉ ሰዎችን ሕይወት በመታደግ ለማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ያስችላል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች ደም የሚያስፈልጋቸው ወገኖች እንዳሉ ያስታወሱት ኃላፊው፤ ደም በመለገስና ሕይወታቸውን በመታደግ ኢትዮጵያ እያስመዘገበች ያለውን ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲያፋጥኑ ማድረግ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ቢሮው የዓለም የቱሪዝም ቀንን ሲያከብር የተለያዩ ሥራዎችን ለማከናወን አቅዶ እየተንቀሳቀሰ ነው ያሉት አቶ ሀፍታይ፤ ከነዚህም ተግባራት አንዱ የሆነውን ደም በመለገስ የሰዎችን ሕይወት የመታደግ ሥራ እየሠራን እንገኛለን ብለዋል፡፡

የዓለም የቱሪዝም ቀንን አስመልክቶ ሁለተኛ ዙር ከጥቅምት ስምንት እስከ 10 ድረስ ሰፊ ደም የመለገስ መርሐግብር እንደሚካሄድ ጠቁመው፣ በሚካሄደውም ንቅናቄ ከሁለት ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ይሳተፋል ተብሎ ይጠበቃል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

አቶ ሀፍታይ አክለውም፤ እየተከበረ በሚገኘው የዓለም የቱሪዝም ቀን የከተማዋን ገፅታ በመገንባት የቱሪዝም ፍሰቱ የተሳለጠ እንዲሆን በትኩረት እየሠራን ነው ብለዋል፡፡


በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ነዋሪ የሆነችው ወጣት ነፃነት እንዳሻው ደም መለገስ ለሀገር ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ጠቁማ፣ ደም በመለገስ የሰዎችን ሕይወት ከማትረፍ ባለፈ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ማፋጠን ተገቢ ነው ብላለች፡፡

ደም መለገስ በጤና ላይ የሚያደርሰው ምንም ዓይነት ጉዳት የለም፤ በደም እጥረት ምክንያት ሕይወታቸውን ለሚያጡ ወገኖች መድረስ ይገባል ስትልም ጠቁማለች፡፡

ወጣቶች በደም መለገስ ተግባር ከመሳተፍ በተጨማሪ የሀገርን ባህል፣ ታሪክና ወግ በመጠበቅ ለትውልድ የማስተላለፍ ሥራ ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸውም አመልክታለች፡፡

‹‹የምንለግሰው ደም የሰዎችን ሕይወት በመታደግ የኢኮኖሚ እድገት እንዲፋጠን ያደርጋል›› ያለው ደግሞ የልደታ ክፍለ ከተማ የወጣቶች ማኅበር ሰብሳቢ ወጣት ግዛቸው ማሞ ነው፡፡

ወጣቱ ደም በመለገስ ተግባር ላይ በመሳተፍ የሰዎችን ሕይወት ሊታደግ ይገባል ሲልም መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡



# አማራ ክልል ከቱሪዝም ዘርፍ 7 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ለማግኘት አቅዷል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ከቱሪዝም ዘርፍ ከ7 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ለማግኘት ማቀዱን የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።

በአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ልማት ዳይሬክተር አቶ መልካሙ አዳም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት ክልሉን ከሚጎበኙ የውጭ ቱሪስቶች ግማሽ ቢሊዮን ብር እና ከሀገር ውስጥ ቱሪስቶች 7 ቢሊዮን ብር በአጠቃላይ 7 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዷል።

አቶ መልካሙ ባለፈው ዓመት 21 ሺህ የነበረውን ክልሉን የጎበኙ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ቁጥር ዘንድሮ ከ80 ሺህ በላይ ለማድረስ የታቀደ መሆኑን ገልጸው፤ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ቁጥርን 20 ሚሊዮን ለማድረስ እንደታቀደ አስታውቀዋል።

በበጀት ዓመቱ በተለይም የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ እና የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት በትኩረት ይሠራል ያሉት አቶ መልካሙ፤ በዚህም የቱሪዝም መሠረተ ልማት አቅርቦት የማስፋፋትና መዳረሻዎችን የማስተዋወቅ ሥራ በስፋት እየተሠራ ነው ብለዋል።

በተለይም በቱሪዝሙ ዘርፍ ከፍተኛ ሚና የሚኖራቸውን ሆቴሎች፣ አስጎብኚ ማኅበራትንና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አሠራራቸውን ለማዘመንና ለማሻሻል ቢሮው ተከታታይነት ያለው የድጋፍና ክትትል ሥራ ይሠራል ነው ያሉት።

በተጨማሪም በኮሮና እና በክልሉ የተፈጠረው ግጭት ምክንያት ይመጣ የነበረ ቱሪስት ቁጥር የቀነሰ መሆኑን ገልጸው፣ ይህንን ለመቅረፍና ለቱሪስቶች ምቹና ሰላማዊ ሁኔታን ለመፍጠር ከባለድርሻ አካላት ጋር እንደሚሠራም ገልጸዋል።

የመረጃ ሥርዓቶችን የማዘመን፣ አዳዲስ የተፈጥሮ የቱሪዝም መስቦችን የማስፋፋትና የማልማት ሥራዎች እንደሚሠሩ ጠቁመው፤ በክልሉ የሚገኙትን የቱሪዝም መዳረሻዎች በማስተዋወቅ እንዲጎበኙና የቆይታ ጊዜን ለማራዘም እንደሚሠራም አመልክተዋል።

በክልሉ ከፍተኛ የቱሪዝም መዳረሻ ከሆኑት መካከል ባህርዳር ከተማ፣ ጎንደር፣ጢስ ዓባይ፣ ላሊበላ፣ የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በዋናነት የሚጠቀሱ መሆናቸውን ገልጸው፤ እንደ ሻደይ፣ ደብረታቦር፣ ገና እና ጥምቀት፣ አዊ ፈረሰኞች፣ መርቆርዮስና መሰል ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላትን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ቱሪስቶች የሚታደሙባቸው መሆኑን ጠቅሰዋል።

በቱሪዝም ልማት ዘርፍ የሥራ ክፍል ውስጥ ለ12ሺህ ዜጎች ቋሚ እና 8 ሺህ ጊዜያዊ የሥራ ዕድል የተፈጠረ መሆኑን ተናግረው፤ ዕቅዱን ለማሳካት ብሎም ክልሉን ሰላማዊ የሆነ የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ ከአጋር አካላት ጋር በቅንጅት በትኩረት ይሠራል ሲሉ ገልጸዋል።

# በክልሉ በዝናብ እጥረት ምክንያት የተጓተተውን የችግኝ ተከላ መርሐግብር ለማካካስ እየተሠራ ነው

**ዳግማዊት አበበ**



አዲስ አበባ፡- በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የሁለተኛ ምዕራፍ አረንጓዴ ዐሻራ የችግኝ ተከላ መርሐግብር በዝናብ እጥረት ምክንያት እንደታሰበው ባይሆንም አሁን ላይ ግን ተጠናክሮ ቀጥሏል ሲል የሐረሪ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የሐረሪ ግብርና ቢሮ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ዳይሬክተር አቶ መሐመድ አባስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የ2015 በጀት ዓመት ሁለተኛው ምዕራፍ የአረንጓዴ ዐሻራ የችግኝ ተከላ መርሐግብር ሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ ሲሠራ ቆይቷል። እስካሁን ባለው ሂደት ሁለት ሚሊዮን የሚሆን ችግኝ መትከል ተችሏል።

ይህም የሆነበት ምክንያት ክልሉ በነሐሴ ወር ማግኘት ያለበትን በቂ ዝናብ በወቅቱ ባለማግኘቱ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በዝናብ እጥረቱ ምክንያት ችግኞቹን ሙሉ በሙሉ ለማፍላት ተቸግረው እንደነበር አንስተዋል። ሆኖም የተፈጠረውን ችግር በመቋቋም ከተተከሉት ችግኞች ውስጥ አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ወይም 70 በመቶ የሚሆኑት ፍራፍሬ ሲሆኑ የተቀሩት ችግኞች ደግሞ የደን ዛፎች ናቸው ብለዋል።

አሁን ላይ ግን የመጨረሻው ዙር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሥራዎች ተጠናክረው ቀጥለዋል፣ እስካሁን ድረስም የታዩ በድርቅ ምክንያት የታየውን ከዕቅድ በታች አፈፃፀም ለማካካስ ችግኞች እየተተከሉ ነው ያሉት አቶ መሐመድ፤ ችግኞቹን በየወረዳዎች የማሰራጨት እና የጉድጓድ ማዘጋጀት ሥራዎችን በትኩረት በመሥራት ባለው አጭር ጊዜ ውስጥ እቅዱን ሙሉ በሙሉ ለማሳካት ርብርብ ላይ እንገኛለን ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በ2016 ዓ.ም ክልሉ ሦስት ሚሊዮን ችግኝ ለማፍላት አቅዷል። ባለፈው በጀት ዓመት የታዩ ችግሮች በተያዘው ዓመት እንዳይደገሙም የተለዩ ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። የነበሩ ክፍተቶችንም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎባቸው ወደ ሥራ የተገባበት ሂደት ነው ያለው። እነዚህ ውይይቶችም ያሉትንና የነበሩትን ችግሮች ይቀርፋሉ ተብሎ ይታመናል ብለዋል።

# «ኢሬቻ ማኅበራዊ ትስስርና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በተለይ በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎችን ይዟል።

በዓሉ በሕዝቦች መካከል ማኅበራዊ ትስስርና አንድነትን በመፍጠር የሀገራችንን ኢኮኖሚ ለማጠናከር ያለው ፋይዳ የጎላ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ቀጀላ ገለጻ፤ ኢሬቻ ከክረምት ወደ መስከረም፣ ከጨለማ ወቅት ወደ ፀሐይ መሸጋገሪያ ወቅት በመሆኑ ባህላዊ እሴቱን በጠበቀ መልኩ ፈጣሪን በማመስገን የሚከበር በዓል ነው።

በዓሉ ማኅበራዊ እሴት ያለውና ሰዎች ተገናኝተው በጋራ የሚያከብሩት የአንድነት መገለጫ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ላለፉት ጊዜያት ተቀያይመው የነበሩ ሰዎች ይቅርታ የሚጠያየቁበት እንዲሁም ያለፈውን ትተው በጋራ የሚያመሰግኑበት በዓል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ኢሬቻ ማኅበራዊ ትስስር በመፍጠር የሕዝቦች አንድነትን ለማጠናከር እንዲሁም የግጭት ማስወገጃ ዘዴ ሆኖ ማገልገል የሚችል በዓል መሆኑን ጠቁመው፤ በዓሉ ከኦሮሞ ሕዝቦች ባሻገር ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችን በአንድነት አቅፎ የሚያሳትፍ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢሬቻን የመሰሉ በዓላትን ማክበርና ሥርዓታቸውን ማጎልበት ማኅበራዊ መስተጋብር የሚያጠናክር መሆኑን በመግለጽ፤ እንደሀገር በቱሪዝምና በኢኮኖሚ አቅም እንድንጎለብት የሚረዳ ነው ብለዋል።

የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሉ አዱኛ በበኩላቸው፤ ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ባህልና እሴቱን በጠበቀ መልኩ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን በጋራ የሚያከብረው በዓል ነው ብለዋል።

በዓሉ ሕዝብ ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት፣ ለመጪው ተስፋን የሚሰንቅበት የምስጋና በዓል ነው ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ኢሬቻን ከሌሎች ወንድም ሕዝቦች ጋር ለማክበር የሚያስችሉ ሃሳቦች ላይ ለመምከር የጉሚ በለል የውይይት መድረክ መዘጋጀቱን ተናግረዋል።

በ34ኛው የጉሚ በለል የውይይት መድረክ በጅማ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ዶክተር ደረጄ ፋፋ የመወያያ ጽሑፍ አቅርበዋል። ከተለያዩ የመንግሥት ተቋማት የተውጣጡ የሥራ ኃላፊዎችን ጨምሮ የዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችም ተገኝተዋል።

# ‹‹የተፈጥሮ ሀብቶቻችንን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ለመገፋፋትና ለመጣላት የሚሆን ጊዜ ስለማይኖረው ያለንን እምቅ ሀብት ሥራ ላይ አውለን የሕዝባችንን ሕይወት ለመለወጥ መትጋት ያስፈልጋል፤ መንግሥትም በየአካባቢው ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም ላይ ለማዋል በቁርጠኝት ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል።

ከሰሞኑ በተደረጉ ጉብኝቶች ለቀጣይ ሥራዎች ግብዓት የሚሆኑ አስደናቂ ሀብቶችን ማየታቸውን ጠቅሰው፤ ሁሉም ዜጎች ሀገራቸውንና በየአካባቢው ያሉ እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመረዳት፣ ለመጠቀምና ለመጠበቅ እንዲተጉ ጥሪ አቅርበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ከሰሞኑ ኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞንና አካባቢው እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የመስክ ጉብኝት ማድረጋቸው ይታወሳል።

# በሰው ዘር መገኛዋ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ለልቡ ቅርብ ነው። የአካባቢውን ቋንቋ ይናገራል። የሕዝቡ ተግባቢነት የአኗኗሩ ቀናነት ልቤን ገዝቶታል ባይ ነው። ይህን ማኅበረሰብ ማገልገል ለመምህሩ በክብርነት ይጠቀሳል።

መምህሩ ገና የህልሙን ያህል አለመሥራቱንም ይናገራል። መቸገርን ያውቀዋልና በከፋ ችግር ላይ የሚገኙትን አይዘነጋም። ለቤተሰቦቻቸው ጭምር የገንዘብ እና የቁሰቁስ ድጋፍ ያደርጋል። ባሳለፍነው ዓመት ከሁለተኛው አጋማሽ ጀምሮ ለትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ምገባ አስጀምሯል።

ለልጃገረዶች ምቹ የትምህርት ቤት ከባቢ የለም። በወር አበባ ወቅት ደግሞ ችግሩ ይበረታል። በዚህ ጊዜ እስከ አምስት ቀን ከትምህርት ገበታ ይቀራሉ። መምህሩ ይህን ሁነት ለመለወጥ ወጠነ። ልጃገረዶች የወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ እንዲያገኙ ሠራ። በቅርብ የሚገኙ ግብአቶችን በመጠቀም እንዲሠራ ኣተነ። በትምህርት ቤቱ ማምረት እንዲቻልም አስተዋፅኦ አደረገ።

በእርሱ ምክንያት የልጃገረዶች ክበብ ተጠናከረ። የወር አበባ በሚያዩበት እና ማረፍ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ የማረፊያ ክፍል ተመቻችቷል። በዚህም የትምህርት ውጤት ተሻሻለ፤ የሚያቋርጡ ተማሪዎች ቁጥር ቀነሰ።

ከሌሎች የትምህርት ቤቱ አመራሮች እና የማኅበረሰብ አባላት ተባባሪ ነው። በትምህርት ቤቱ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲሰጥ ታትሯል።

በእጃቸው ማጠር ትምህርት ቤት መምጣት ላልቻሉ ደጋፊ ነው። ትምህርት ቤቱ አመቺ እንዲሆንላቸው ሠርቷል። የተሻለ ግልጋሎት እንዲሰጥም አስተዋፅኦ አድርጓል። መምህራንን እና የማኅበረሰብ ተወካዮችን ያስተባብራል። ከልጃገረዶች ክለብ ጋርም ተባባሪ ነው። ከአቅም በላይ በሆኑ ጉዳዮች ተስፋ ቆርጦ አይቀመጥም።

በቅርቡ ካሉ አጋዦች ጋር ይተባበራል። ማኅበረሰቡ በልጃገረዶች ትምህርት ላይ በጎ አመለካከት እንዲኖረው ጥሯል። የአካል ጉዳተኛ ልጆች ያሏቸውን ቤተሰቦች ያወያያል። ሕዝቡ በአካል ጉዳተኝነት ላይ ያለውን አመለካከት የተሻለ አድርጓል። በዚህም ወላጆች አካል ጉዳተኛ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ ሆኗል።

ከአሳይታ ሆስፒታል ጋርም ተባብሮ ይሠራል። የአካል ጉዳተኝነት ላይ የሚታይ ሥራ ተሠርቷል። ተማሪዎቹ ምቹ የትምህርት አካባቢ እና ድጋፍ እንዲያገኙ ተችሏል። ከ30 በላይ የሚሆኑ ተደራራቢ ጉዳተኝነት ያላቸው ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ እየተከታተሉ ይገኛሉ።

በማኅበረሰቡ ከተከበሩ ሰዎች ጋር አብሮ ሠርቷል። የሀገር ሽማግሌ ጋሽ መሐመድ ዓሊ አንዱ ናቸው። የትምህርት ቤቱ ምክትል ርዕሰ መምህር ከሆነው ከአቶ ጂላኒ ዓሊ ጋርም በትብብር ይሠራል።

መምህር አንዋርን የሴት ተማሪዎችን የመማር ጥቅምን የተረዱት ሁሉ ያግዙታል። የሴት ተማሪዎች ህልም እንዳይጨናገፍ ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል። ያለዕድሜ ጋብቻ ላይ ሥራ ሠርቷል። በግሉም በቡድንም ሆኖ ጎጂ ባህሎችን ተዋግቷል። ከባል እና የባል ወላጆች ጋር ትምህርቷን እንዲደግፉ ስምምነት ተፈራርሟል።

ከአቅም በላይ ሆኖ ያለ ዕድሜ ጋብቻ የፈፀሙትን ልጃገረዶች በዚያው እንዳይቀሩ አድርጓል። የባል ወገኖችን በማሳመን ትምህርት ያቋረጡ ወደ ገበታቸው ተመልሰዋል። ያገቡም ሆነ ልጅ የወለዱ ሴት ተማሪዎች እንዲመለሱ ተደርጓል።

ልጃገረዶች በትዳር ላይ ሆነው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ አድርጓል። ከቤት ወደ ትምህርት ቤት በሚመላለሱበት ችግር እንዳይገጥማቸው ጥበቃ ያደርጋሉ። ለአካል ጉዳተኛና ሴት ተማሪዎች ትምህርት ገበታ እንዲገኙ መንገድ ጠርጓል። የበዛ ቁጥር ላላቸው ተማሪዎች ሁሉን አካታች የትምህርት አገልግሎት እንዲሰጥ አስችሏል።

ለአፋርና ከባቢው ለሠራው መልካም ሥራ እውቅና ተሰጥቶታል። የ11ኛው የበጎ ሰው ሽልማት በመምህርነት ዘርፍ በመታጨትም ምስጋና ተችሮታል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በመመካከር ሰላማችንን በጽኑ መሰረት ላይ እናኑር!

እኛ ኢትዮጵያውያን በአንደበታችን የሰላምን ከፍ ያለ ዋጋ እንተርካለን፤ ስለ ሰላም የሁሉ ነገር መሰረትነት እንናገራለን፤ ስለ ሰላም የፈጣሪ መገለጫነት እንመሰክራለን። በተለይም እንደ ሀገርና ሕዝብ በግጭትና ጦርነት ምክንያት ብዙ ዋጋ እንደከፈለ ሕዝብ የሰላምን ዋጋ በመገንዘብ ረገድ የምንሰጠው ዋጋ እጅግ ከፍ ያለ ነው።

"ሰላምን እሻት፣ ተከተላትም" እንዲል ቃሉ፤ ታዲያ ይህችን በብዙ የምናወራላትን ሰላም፣ በምናወራላት ልክ ምን ያህል ተገንዝበናት በመካከላችን ልናመላልሳት፤ በፀና መሰረት ላይ ልናኖራት፤ እንዳትናወጥ አድርገን ከእኛ ጋር ልናዘልቃት እየሠራን ነው? የሚለው ላይ ሁሉም ራሱን ሊጠይቅ የሚገባው ጉዳይ ነው።

ምክንያቱም ሰላም ከመሰረቷ የራስን፣ የቤተሰብን፣ የጎረቤትን፣ የአካባቢን፣ የማሕበረሰብን፣ የሀገርና አሕጉርን፣ ብሎም የዓለምን ጸጥታ የምትወስን ናትና። ለሰው ልጆች ዕረፍት የምትሰጥ፣ ርጋታን የምታላብስ፣ ርካታን የምታጎናጽፍ፤ በዚህ ሁሉ መካከል ደግሞ የሰው ልጆችን በፍቅርና በአንድነት ተቻችሎ አብሮ የመኖርን ከፍ ያለ ስሜትና ልዕልና የምታስገኝ ሰገነት ናት።

ለምሳሌ፣ ሰላምን 'የጦርነት አለመኖር፣ ወይም ያለመረበሽ ወይም ነፃነት ነው" በማለት የሚገልጹ መዛግብትና ምሁራን አሉ። ይሄ ነጻነት ባለበት ቦታ ደግሞ፣ 'እርቅ፣ ፀጥታ፣ እርጋታ፣...' በእጅጉ ጎልተው የሚስተዋሉ የሰላም መገለጫዎች ስለመሆናቸውም አያይዘው ይዘረዝራሉ።

በሌላ በኩል፣ "ሰላም ማለት የግጭት አለመኖር ማለት አይደለም" ሲሉ የሚሞግቱ የዘርፉ ምሁራንም አሉ። እነዚህ ደግሞ ሰላምን ከሕሊና እረፍት እና ፀጥታ ማግኘት፣ ከሁከት ከሽብርና ከስቀቀን መራቅ፣ ከአንድነትና ስምምነት መኖር ጋር አዛምደው ይገልጹታል። የግጭት አለመኖር የሠላም መኖር ምልክት እንጂ በራሱ ሰላም አይደለም የሚል ጭብጥም ያቀርባሉ።

እነዚህ በሁለቱም መንገድ የሚነሱ ሀሳቦች የተለያዩ ይምሰሉ እንጂ ማጠንጠኛቸውም፤ መዳረሻቸውም አንድ ነው፤ ሰላም። የሰው ልጆች ደህንነት፤ የሕብረተሰብ አብሮነትና እረፍት፣ ሙሉነት፣ ስኬት፣ ሁለንተናዊ ደህንነት፣... የሚሉትን የሰውና የማሕበረሰብ ሰላም ጉዳዮችን ይመለከታሉ።

ታዲያ ይህችን የዕረፍት ሰገነት የሆነችውን ሰላም በጽኑ መሰረት ላይ ማኖር፤ ዘላቂ በሆነ ውቅር ላይ ማጽናት ደግሞ ከሁሉም ዜጋ ይጠበቃል። በተለይ እንደ እኛ በሰላም እጦት ዋጋ ለከፈለ፤ በጦርነት አረር ለተመታ፤ በመፈናቀልና በርስ በርስ ግጭት ለታመሰ፤ ወንድማማቾችን በተቃርኖ ጎራ አሰልፎ ሰይፍ ለተማዘዘ፤ ዛሬም ድረስ በዚሁ ጠባሳ ምክንያት እየተናቆረ ላለ ሕዝብ ይሄን ማድረግ ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም።

እኛን ኢትዮጵያውያንንም የሚመለከተን ይሄው ነው፤ በፀጥታ እና በሕሊና እረፍት ውስጥ መኖር። በአብሮነትና በሕብረት መድመቅ፤ በሰላም በስኬት ጎዳና ላይ መመላለስ፤ በፍቅር ወደ ይቅርታ እና እርቅ ማምራት፤ በወንድማማችነት ስሜት በጋራ ቁጭ ብሎ መነጋገርና ችግሮችን መሻገር።

ዛሬ የሚያስፈልገን ይሄን መሰሉ የሰላም መንገድ ነው። ይሄን ዓይነቱ የሰላም ማምጫ ሥርዓት ነው። መደማመጥ፣ መከባበርና በሃሳብ ብዝኃነት አምኖ ለአብሮነታችን ጋሻ የሚሆን ጡብ ከሁላችንም አንደበት እንዲወጣ፤ በሁላችንም እጅ እንዲሰራ ማድረግ ነው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽንም በአዋጅ ተቋቁሞ ወደ ስራ ሲገባ ይሄንኑ ማድረግን ታሳቢ በማድረግ ነው። የሚሠራውም የትናትን ጠባሳዎችን ማከም፤ ስብራቶችን መጠገን፤ ቂምና ቁርሾን መሻር፤ ፍቅርና አብሮነትን ማጽናት፤ በይቅርታና እርቅ ጠብንና የመጠላላት ግድግዳን መናድ፤ ስለ ሰላም እውን መሆን ሁሉን አቀፍ ሥራ ማከናወንን ታላሚ አድርጎ ነው።

ኮሚሽኑ ታዲያ ኢትዮጵያውያን ስለ ሰላማቸው ቁጭ ብለው እንዲመክሩ መድረክ ይፈጥርላቸዋል እንጂ፣ አንደበት ሆኖ አይናገርላቸውም። የአብሮነትን ልዕልና ተረድተው ስለ ሕብረብሔራዊ አንድነታቸው ሲሉ ይቅርታና እርቅን ሀብታቸው እንዲያደርጉ በትር አያነሳባቸውም።

ነገር ግን ይሄን እንዲያደርጉ መድረክ ይፈጥርላቸዋል፤ የሰላምን መንገድና ልዕልና ያመላክታቸዋል፤ ስለ እርቅና ይቅርታ፣ ስለ ፍቅርና አብሮነት፣ በቀና ልብና ሕሊና ቁጭ ብሎ መምከር ስላለው ከፍ ያለ ፋይዳ፤... በማስገንዘብ ወደ ንግግርና ሰላም እንዲያመሩ ሁኔታዎችን ያመቻችላቸዋል።

ይሄ ማለት በተፈጠረው ዕድል ተጠቅሞ ለመመካከር በጋራ የመቀመጥ፤ ወደ አንድነት የሚያመጡ መልካም ሃሳቦችን የማዋጣት፤ የሚያለያዩ እና በታሪክ ሂደት የተፈጠሩ ችግሮችን በግልጽ ተነጋግሮ በሰላም የመፍታት፤ በእርቅም ለመሻገር ቁርጠኛ የመሆን ትልቁ የቤት ሥራ ያለው እኛው ሕዝቦቹ ላይ ነው።

በመሆኑም በሰከነ አዕምሮ ተነጋግሮ፤ በንጹሕ ኅሊና ተወያይቶ፤ በቅን ልቡና አቀራራቢ ሃሳቦችን ገዝቶ፤ ከትናንት እስከ ዛሬ ዋጋ ያስከፈሉንን ጉዳዮች በማስወገድ፤ ከትናንት እስከዛሬ ለአብሮነታችን መሰረት የሆኑ እሴቶችን የበለጠ በማላቅ፣ የራቀንን ሰላም ለማቅረብ፤ የጠፋብን የሕሊና እረፍት ለመመለስ መትጋት ይኖርብናል።

ስለሆነም በተዘጋጀልን የምክክር መድረክ ላይ ስንሰየም፣ ዘመናትን ዋጋ ያስከፈለንን የሰላም እጦት በሰላም ለመተካት፤ በመምከርም ሰላማችንን በጽኑ መሰረት ላይ ለማኖርና ለማዝለቅ፤ እኛም ከሰላሙ ሰገነት ስንገኝ በብዙ እንደምናተርፍ አምነን ሊሆን ይገባል!

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ልጆቻችን ባወረስናቸው ችግርና መከራ ሳይሆን በበጎ ነገሮች እየኮሩ እንዲኖሩ

ወጋሶ

በርካታ የዓለም አገራት በትርምስና በግጭት ውስጥ አልፈዋል፤ እያለፉም ይገኛሉ። ይሁንና ጉዳዩ የአፍሪካ አገራት ላይ አይሎና ገዝፎ ይስተዋላል። በእርግጥ በአህጉርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለትርምስም ሆነ ለግጭት የሚቀመጥ ምክንያት ይኖራሉ። እርስ በእርስ የሚጋጨውም አካል ቢሆን ለመጋጨቱ በምክንያትነት የሚያስቀምጠው የራሱ የሆነ ሰበብ አለው።

ለግጭቱና ሰላም መታጣቱ ዋናው ምክንያት የሚባለው ጉዳይ እንደየአገራቱ ነባራዊ ሁኔታ ይለያይ እንጂ አብዛኞቹ ከሚደረድሯቸው ምክንያቶች መካከል ግንባር ቀደሞቹ የፖለቲካ፣ የብሔር፣ የጎሳ፣ የኃይማኖት ልዩነቶችና መሰል ጉዳዮች ናቸው። ይሁንና እነዚህ ችግሮች በአብዛኛው ሽፋን እንጂ እውነተኛ የግጭት መንስዔ ሊሆኑ የሚችሉ እንዳልሆኑ ይታመናል ።

በአህጉሪቱ የሚገኙ ለራሳቸው የተለያዩ ስያሜ የሚሰጡ ግለሰቦችና ቡድኖች የራሳቸውን ፍላጎት ለማሳካት ሲሉ ለሚያነሷቸው ግጭቶች ብሔራቸውን፣ ቋንቋቸውን እንዲሁም ኃይማኖታቸውን በምክንያትነት መጥቀስ የተለመደ ነው። በተለይ በአፍሪካ አገራት፤ መሰል ሰበብ የተለመደና የአህጉሪቱን ህዝቦች እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ብዙ ዋጋ እያስከፈለ የሚገኝ እርግማን ነው።

የሚያሳዝነው ችግሮቹ ብዙዎችን ለህልፈት ከዳረጉ፤ ከፍተኛ የሆነ የሀብት ውድመት ካስከተሉ በኋላ ችግሩን ለመፍታት በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት ወደ ውይይት ብሎም በድርድር መግባታቸው ነው። ይህም ቢሆን በተሰጠ የሰላም ፈላጊነት መንፈስ ስለማይገራ ብዙም ስኬታማ ሲሆን አይታም።

ይህ ማለት ግን ችግሮቻቸውን በድርድር መፍታት የቻሉ ሀገራት የሉም ማለት አይደለም ። ለዚህ ደቡብ አፍሪካ መጥቀስ ይቻላል። እንደሀገር ደቡብ አፍሪካውያን የገቡበትን የከፋ ሀገራ ዊ ስጋት በእርቅ መንገድ መፍታት በመቻል ከዓለም ተጨባጭ ምሳሌ መሆን ችለዋል። ላገኙት ስኬት ጥረዋል፣ በብዙ ደክመዋል ።

ደቡብ አፍሪካውያን ከብዙ የመስዋዕትነት ትግል በኋላ የአፓርታይድ ስርዓት በመገርሰስ፤ ቀጣዩን ዘመን ከቂምና በቀል ነጻ አድርገው ሀገራቸውን እንደሀገር በሰላም ለማስቀጠል፤ የቀድሞ እስከፊ ታሪካቸውን በእርቅ ዘግተዋል። "የሐቅና የእርቀ ሰላም ኮሚሽን" የተባለ ተቋም መስርተው ስለ እርቅ በጽናት ተንቀሳቅሰዋል ። በዚህም ደቡብ አፍሪካውያን እውነትን በመናገር እርቅን ማውረድ ችለዋል።

በዚህ አካሄድ የነበረውን ቂምና ቁርሾ እንዲሁም ጥላቻና አለመተማመን በእርቀ ሰላም በመቋጨቱ ዛሬ ደቡብ አፍሪካ ሰላሟ ሰፍኖ በኢኮኖሚዋም ጠንካራና ከአህጉራችንም ፊተኛው መስመር ላይ የተሰለፈች ሀገር ለመሆን በቅታለች። ይህ ዝም ብሎ ሳይሆን ስለ ሰላም እርቅ በተከፈለ ከፍ ያለ ዋጋ የመጣ ስኬት ስለመሆኑ መላው ዓለም የሚያውቀው አደባባይ የሞቀ እውነታ ነው።

በኛም ሀገር ወደ ግጭት የሚወስዱ ሀገራዊ አለመግባባቶችን በእርቅና በድርድር ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፤ ለዚህም "የእርቀ ሰላም ኮሚሽን" በሚል በአዋጅ ቁጥር 1102/2011 ዓ.ም ተቋቁሞ ሲንቀሳቀስ ነበር። ከዚህ ባለፈም አሁን ላይ፤/በ2014 ዓ.ም"የኢትየጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጁ ወጥቶ ፣ ኮሚሽኑ ተቋቁሞ ወደ ስራ የገባበት ሁኔታ አለ ።

ኮሚሽኑ የተቋቋመው በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያዩ የፖለቲካና የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል መሰረታዊ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚታየውን የሐሳብ ልዩነቶችና አለመግባባቶች እንዲሁም የታሪክ ትርክቶች ዙሪያ በውይይት እና ምክክር ወደ አንድ መግባባት ለመድረስ ነው ።

ኮሚሽኑ ከፖለቲካ ወገንተኝነት፣ ከማንኛውም የመንግስት ወይም ሌላ አካል ተጽዕኖ ነጻ ወደ ስራ ከገባ ውሎ አድሯል፣ በአሁኑ ወቅትም የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቶ የውይይት ተሳታፊዎች ልየታና ሌሎች ጉዳዮችን በማከናወን ላይ ይገኛል።

ኮሚሽኑ ወደ ግጭት ሊወስዱ የሚችሉ አለመግባባቶችንና ታሪክ ትርክቶችን በውይይት ለመፍታት ለሚያደርገው ጥረት ሁሉም ዜጋ ኃላፊነት እንዳለበት ይታመናል ። የተቋሙ ስራ ስኬታማ እንዲሆን ተባባሪ በመሆን ከሁሉም በላይ ተጠቃሚ የሚሆነው ትውልዱ ነው ። ለዚህም ያሉንን መልካም የእርቅና መሰል አገራዊ እሴቶቻችን በአግባቡ መጠቀምም አስፈላጊነቱ ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም።

> **ሰ**ላም ለአንድ ሀገርና ህዝብ ካለው ሁለንተናዊ አስተዋጽኦ አንጻር፤ ሀገራዊ ሰላማችንን ለማጽናት ባለን አቅም ሁሉ ልንተጋ ይገባል። እልህ ከመጋባት ወጥተን አንዳችን ለሌላችን ምርኩዝ መሆን ይጠበቅብናል። በደል ቆጣሪ ከመሆን ወጥተን ይቅር ባይ ልንሆን ይገባል። ቂም ገዝግዞ የሚጥል ነቀርሳ ነው። የቂም ነቀርሳ ሊታከም የሚችለው ይቅር በመባባል ብቻ ነው ለዚህ ደግሞ ሁሌም ዝግጁ እንሁን

በእርግጥም መመካከር መልካም ነው። ምክክር ሲባል የጋራ መፍትሔ ፍለጋ ላይ ያተኮረ የሐሳብ ልውውጡ ነው። በዚህ መልኩ የሚደረግ መመካከር ያማረ ውጤት ይኖረዋል። ውጤታማነቱ ደግሞ ዘላቂ ሰላም እንዲኖር የሚያስችል ሀገራዊ አውድ ተፈጠረ ማለት ነው ፤ ይህ ደግሞ ለምንፈልገው ልማታችን አልፋና ኦሜጋ ነው ። ከዚህም ባለፈ ቅቡልነት ያለው አገረ መንግስት ለመገንባትም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

ስለሀገራዊ ዘላቂ ሰላም ፤ ብሄራዊ ምክክሩን በቀና መንፈስ ማካሄድ ወሳኝ ነው ፤ ለዚህ ደግሞ ከእኛ ከዋንኛዎቹ ባለጉዳዮች /ከዜጎች የሚጠበቀው ብዙ ነው። ከሁሉም በላይ የእኛን ቅንነት ለእውነትና ለሃቅ መቆምን የሚጠይቅ ነው።

ሰላም ለአንድ ሀገርና ህዝብ ካለው ሁለንተናዊ አስተዋጽኦ አንጻር፤ ሀገራዊ ሰላማችንን ለማጽናት ባለን አቅም ሁሉ ልንተጋ ይገባል። እልህ ከመጋባት ወጥተን አንዳችን ለሌላችን ምርኩዝ መሆን ይጠበቅብናል። በደል ቆጣሪ ከመሆን ወጥተን ይቅር ባይ ልንሆን ይገባል። ቂም ገዝግዞ የሚጥል ነቀርሳ ነው። የቂም ነቀርሳ ሊታከም የሚችለው ይቅር በመባባል ብቻ ነው ለዚህ ደግሞ ሁሌም ዝግጁ እንሁን።

ለሰላም ዝቅ እንበል። ለሰላም ዝቅ ባልን ልክ ለልጆቻችን ለልጅ ልጆቻችን የምናስቀምጣት አገር ከቂም በቀል የጸዳች የለማችና የበለጸገች ትሆናለች። በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን ለሰላም ዝቅ ማለት ነገ ከፍ የማለታችን ምስጢር እንደሚሆን ተረድተን እራሳችን ልናዘጋጅ ይገባል።

እንደ አንድ አገር ህዝቦች ተሳስበን ተዋደን፤ አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ተባብለው እንድንኖር ከሁሉም በላይ ለሰላምና እርቅ ዝቅ ብለን ነጋችንን ብሩህ ማድረግ አለብን። ልጆቻችን ባወረስናቸው ችግርና መከራ ሲታመሱ የሚኖሩ ሳይሆኑ፣ ባስቀመጥንላቸው በጎ ነገር እየኮሩ እሱን እያስቀጠሉ ሰላማዊ አገር የሚመሩ እንዲሆኑ ሁላችንም ስለ ሰላም በኃላፊነት መንፈስ እንቀሳቀስ ።

## ነፃ ሃሳብ

# ከትላንት ያደሩ ወረቶቻችን የዛሬ ስንቆቻችን ናቸው

ሀገር በአንድ ጀንበር ተገንብታ አታድርም። ትላንት ለዛሬ አሻግሮ በሚሰጠውና ዛሬም በተራው በሚያቀብለው ወረት ነው ሀገር እየተገነባች የምትጓዘው። በአጭር አማርኛ ዛሬ ያለትላንት የለም፤ ነገም ያለ ዛሬ ህልውና የለውም።

አዲስ የገባው 2016 ዓ.ም ያለ 2015 ዓ.ም እውን ሊሆን አይችልም። በ2015 በበጎም ሆነ በክፉ የተከሰቱ ጉዳዮች በ2016 ዓ.ም በበጎም ሆነ በክፉ አሻራ ማሳረፋቸው አይቀሬ ነው። ስለዚህም በ2015 ዓ.ም እንደ ሀገር ያገኘናቸው ድሎችና ያጋጠሙን ተግዳሮቶች አዲስ በያዝነው ዓመት ላይ የራሳቸውን አሻራ ማሳደራቸው አይቀሬ ነው።

እንደ ሀገር የነበሩን ጥንካሬዎች ለመጪው ጊዜ እርሾ ሆነው ያበረቱናል። ድክመቶቻችንም እንዲሁ ታርመው ለነገ ጥንካሬያችን ምንጭ ይሆኑናል። በአጠቃላይ ጥንካሬዎቻችንን አጎልብተን፤ ድክመቶቻችን ቀርፈን የተሻለች ሀገር እንደትኖረን እንደ መልካም እድል ሆነው ያገለግሉናል።

የሸኘነው 2105 ዓ.ም እንደ ሀገር በርካታ ውጤቶች ያገኘንበትና በዚያው መጠንም የተፈተንበት ዓመት ነው። በ2105 ዓ.ም ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረክ ጎልታ የወጣችበት፤ በግብርና ምርት ውጤት ያመጣችበት፤ የድሆችን እንባ ያበሰችበትና ሰላምንም ለማጽናት ብዙ ርቀት የተጓዘችበት ነው።

ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ለሁለት ዓመታት ሲካሄድ የነበረው ደም አፋሳሽ ጦርነት የቆመበትና የፕሪቶርያው ስምምነት የተፈረመበት ታሪካዊ ቀን ነው። የፕሪቶሪያ ስምምነት ኢትዮጵያውያን ያለማንም ጣልቃ ገብነት የሀገራችውን ሰላም ማስጠበቅ እንደሚችሉ ያሳየና በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድም ግርማ ሞገስን ያላበሰ ታሪካዊ ክንውን ነው።

ይህም ስምምነት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ሲካሄድ የነበረውን ጦርነት አስተማማኝ በሆነ መልኩ የቋጨና ሞት፤ የአካል መጉደል፤ ስደትነና መፈናቀልን በማስቀረት ኢትዮጵያ ፊቷን ወደ ልማት እንድትመልስ ያስቻለ ነው። ይህ ስምምነት ኢትዮጵያውያን የጦርነት ብቻ ሳይሆን የሰላም ጀግኖች እንደሆኑ ያሳየና በሀገሪቱ ታሪክም አዲስ ታሪክ እንዲጻፍ ያስቻለ ነው።

2015 ዓ.ም ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክ ጎልታ የወጣችበት ዓመት ነበር ማለትም ይቻላል። በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ፣ ከተደረገው የሰላም ስምምነት በመከተል ከዓለም አቀፍ ተቋማትና ከአውሮፓ አገራት ጋር ተቀዛቅዞ የነበረው ግንኙነት በመልካም ሁኔታ መቀጠል መጀመሩ በዓመቱ ከተከናወኑ ዓበይት የዲፕሎማሲ ድሎች መካከል የሚዘከር ነው።

ከዲፕሎማሲያዊ ድሎቹ መካከል ተጠቃሽ የሆነው አንዱ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ኃላፊነትን ከያዙ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የሥራ ጉብኝት ያደረጉት አንቶኒ ብሊንከን፣ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትርን ጨምሮ ከተለያዩ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር ስለሀገራቱ ቀጣይ ግንኙነት መወያየታቸው ነው።

ሌላው ተጠቃሽ የሚሆነው ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በጣሊያን ሮም በተካሄዱ የተባበሩት መንግሥታት የልማትና ፍልሰት ጉባዔ እንዲሁም የዓለም ምግብ ድርጅት የምግብ ሥርዓት ስብሰባ ላይ ተሳትፈው ኢትዮጵያ በምግብ ራስን በመቻልና ሕገ ወጥ ስደትን በመከላከል በኩል ያላትን ልምድ ማካፈላቸው ነው። ከጉባዔው ጎን ለጎን ከተለያዩ አገራት ጋር የሁለትዮሽ ውይይትም አድርገዋል።

የዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት አጃይ ባንጋ ባሳለፍነው ዓመት ኢትዮጵያ በመምጣት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ተነጋግረዋል። የፕሬዚዳንቱ ጉብኝትም የዓለም ባንክ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን የትብብር አድማስ በማስፋት ለኢኮኖሚ እድገታችን በኮንሴሽናል ፋይናንስ፣ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን በኩል ጠንካራ የኢንቨስትመንት ፋይናንስ አቅርቦት በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል። የተባበሩት አረብ ኢሚሬቶች ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት አዲስ አበባ መጥተው 17 ስምምነቶችን የተፈራረሙትም በዚሁ ዓመት ነው።

በሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም በአንድ ጀንበር 569 ሚሊዮን ችግኝ በመትከል ዓለምን በሌላ አዲስ ታሪክ ጉድ ያሰኙት በዚሁ ዓመት ነው። እንደ ሀገገርም ባለፉት አራት ዓመታት ከ31 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል በበረሃማነትና በአየር ጸባይ ለምትሰቃየው ዓለማችን መድህን መሆን ችለናል።

ስንዴ ከራስ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያም የቀረበው በዚሁ በሸኘነው 2015 ዓ.ም ነው። በዚህ ዓመት ብቻ 32 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ መቅረቡ የዚሁ ስኬት አንዱ ማሳያ ነው። በሩዝ ዘርፍም እየተከናወነ ያለው ተግባርም ኢትዮጵያን ከሩዝ ተቀባይነት ወደ አስመጪነት የሚያሸጋግራት ነው።

ኢትዮጵያ እንደ ስንዴው ሁሉ ለሩዝ ምርት ትኩረት በመስጠት ከሀገራዊ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያ ለመላክ በትኩረት በመስራት ላይ ትገኛለች። በተለይም ሀገሪቱ ለሩዝ ምርት ተስማሚ የሆነ የአየር ጸባይና ምቹ መሬት ያላት መሆኑ ያቀደችውን ወደ ተግባር ለመለወጥ እንደማያዳግታት የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ።

ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለከትውም፤ በኢትዮጵያ 5 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር በሩዝ መልማት የሚችል መሬት ቢኖርም በየዓመቱ ከ200 ሺህ ቶን በላይ ሩዝ ወደ ሃገር ውስጥ በማስገባት በየዓመቱ 200 ሚሊዮን ዶላር ወጭ ታደርጋለች።

በኢትዮጵያ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ስርዓት መተግበር ከጀመረ ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ መንግስት ፊቱን ወደ ሩዝ ምርት በማዞር በአጭር ጊዜ ውስጥ አበረታች ውጤቶች መመዝገብ ጀምረዋል።

አሁን ላይ ሩዝ በስፋት የሚመረተው በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉምዝ እና ትግራይ ክልሎች ሲሆን በዘንድሮው 2015/2016 የምርት ዘመን በአማራ 150 ሺህ ሄክታር መሬት በሩዝ በመሸፈን 8 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው።

በተመሳሳይም በኦሮሚያ ከ1 ሚሊዮን ሄክታር በላይ በሩዝ ለመሸፈን ታቅዶ እስካሁን 700ሺ ሄክታሩን ማሳካት ተችሏል። የሁለቱ ክልሎች እንቅስቃሴ ብቻ በሀገር ውስጥ ለምግብ ፍጆታነት የሚጠበቀውን ከ6ሚሊዮን ያልበለጠ ፍላጎት በመሸፈን ቀሪውን ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ነው።

የ2015 ዓ.ም ትሩፋቶች ከሆኑት ውስጥ የአባይ ግድብ አራተኛ የውሀ ሙሌት ተጠቃሽ ነው። በዚህ ትውልድ ጠንሳሽነት ግንባታው በመገባደድ ላይ የደረሰው የአባይ ግድብ በርካታ ፈተናዎችና አሜካላዎች ቢገጥሙትም በዚህ ትውልድ አይበገሬነት ዛሬ ከራስ አልፎ ለጎረቤት ሀገራት ብርሃን መሆን ችሏል። በ2105 ዓ.ም በተሰሩ ስራዎችም በያዝነው ዓመት ተጨማሪ አምስት ተርባይኖችን ወደ ስራ የማስገባት ስራዎች ይከናወናሉ። በአጠቃላይም በዚህ ዓመት ብቻ ሰባት ተርባይኖች አገልግሎት ይሰጣሉ።

በ2015 ዓ.ም እንደ ሀገር ከተገኙ የዲፕሎማሲ ስኬቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ደግሞ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል መሆን መቻሏ ነው። በተሰሩት እልህ አስጨራሽ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች ብዙዎች የተመኙትን የብሪክስ አባልነት ኢትዮጵያውያን ማሳካት ችለዋል። ይህም ለሀገሪቱ በርካታ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞች ይዞ የሚመጣ ነው።

የለውጡ መንግስት ሀገሪቱን መምራት ከጀመረ ወዲህ እየጎለበቱ ከመጡ መልካም ተግባራት መካከል መረዳዳትና መደጋገፍ አንዱ ነው። በተለይም ጧሪ እና ደጋፊ የሌላቸውን ወገኖች አንዱ ባህል እየሖነ የመጣ መልካም ተግባር ነው። ይህም የበጎ ፈቃድ ስራ በ2015 ዓ.ም ተጠናክሮ የቀጠለበት ዓመት ነበር።

የ20ሺ አቅመ ደካማ ቤቶች ታድሰው በአዲሱ ዓመትም ቤት ለእንቦሳ ተብለዋል። ብዙዎችም በማዕድ ማጋራትም አዲሱን ዓመት ተደስተው ውለዋል። በአዲሱ ዓመት ዋዜማ የአዲስ አበባ አስተዳደር ብቻውን ከ450ሺ በላይ ለሚሆኑ አቅመ ደካሞች ማዕድ አጋርቷል።

በ2105 ዓ.ም የአላላ ኬላ የቱሪስት ማዕከል ተገባዶ ለአገልግሎት ክፍት ሆኗል። የኮይሻ፤ የጎርጎራ፤ የወንጪ፤ የቱሪስት መስህቦች እየተገባደዱ ነው። በአዲስ አበባም እየተከናወኑ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶች መጪው ጊዜ ብሩህ መሆኑን ያመላክታሉ።

በነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም. በሀንጋሪ ዋና ከተማ ቡዳፔስት በተዘጋጀው 19ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ በዘጠኝ ሜዳሊያ ከዓለም ስድስተኛ ሆና አጠናቃለች። በሴቶች 10ሺህ ሜትር ውድድር አትሌቶቻችን ከአንድ እስከ ሶስት ተከታትለው በመግባት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች "አረንጓዴ ጎርፍ" በሚል የሚታወቁበትን የአጨራረስ ስልት ዳግም በማሳየት አኩርተውናል።

በዚህ ውጤት ጉዳፍ ፀጋይ ወርቅ፣ ለተሰንበት ግደይ ብር እንዲሁም እጅጋየሁ ታየ ነሐስ አምጥተዋል። በሴቶች ማራቶን ደግሞ አማኔ በሪሶ እና ጎተይቶም ገብረስላሴ ተከታትለው በመግባት የወርቅ እና ብር ሜዳሊያ አግኝተዋል። በወንዶች 10 ሺህ ሜትር ውድድር ሰለሞን ባረጋ ሶስተኛ በመውጣት ለሀገሩ የነሐስ ሜዳሊያ ሲያስገኝ፤ በሴቶች 1500 ሜትር ድርቤ ወልተጂ ሁለተኛ ሆና የብር ሜዳሊያ አስገኝታለች።

በወንዶች 3 ሺህ ሜትር መሰናክል የዓለም ክብረ-ወሰን ባለቤቱ ለሜቻ ግርማ ሁለተኛ ሆኖ በማጠናቀቅ ብር ማግኘት ችሏል። በመጨረሻው ቀን በተካሄደ የወንዶች ማራቶን ልዑል ገብረስላሴ ሶስተኛ ሆኖ በማጠናቀቅ ነሐስ አግኝቷል። ኢትዮጵያ በጠቅላላው ዘጠኝ ሜዳሊያዎችን ሰብስባ ከአፍሪካ ሁለተኛ ከዓለም ስድስተኛ ሆና አጠናቃለች።

ከእነዚሁ ስኬቶች ጎን ለጎን ጦርነት፤ ግጭት፤ መፈናቀል፤ ስደት፤ ድርቅ፤ የመሳሰሉት ችግሮች ኢትዮጵያን ፈትነዋታል። አለመተማመን፤ መወነጃጀል፤ ጥላቻና ቂምም የፖለቲካችን አንዱ መለያ ሆኖ አብሮን ቆይቷል። ይህም ሁኔታ በተወሰኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ጦርነት እንዲቀሰቀስ፤ ግጭት እንዲበራከት፤ ሞትና የንብረት ውድመት እንዲከሰት አድርጓል። በዚህም በርካቶች ሕይወታቸውን አጥተዋል፤ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ ተሰደዋል።

ይህ ታሪክ ግን አንድ ቦታ ማብቃት አለበት። የሕዳሴ ግድብን የገነቡ ክንዶች፤ በአንድ ጀንበር ከ569 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን የተከሉ እጆች፤ የተራቡና የታረዙ ወገኖችን የታደጉ ስብናዎች ለግጭትና ለጦርነት ቦታ ሊኖራቸው አይገባም።

ስለዚህም የመገሻጨት፤ የመጠፋፋት እና የመገዳዳል ታሪካችን ሊዘጋ ይገባል። አሁን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ግጭት፤ ጦርነትና መወነጃጀል ሳይሆን ውይይትና ምክክር ብቻ ነው። ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህልም እንደሀገር ሊጎለብት ይገባል። የስልጣኔም አንዱ መለኪያም ይኸው ነውና። በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ሥራ ውስጥም ሆነ በሌሎች መስኮች የተሰማሩ ወገኖች፣ ለውይይት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።

ኢትዮጵያ ከፊቷ የተጋረጡ በርካታ ችግሮች ያሉባት አገር ናት። የአገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ጊዜ መስጠት አለባቸው። ጽንፍ ለጽንፍ ሆኖ ቃላት መወራወርና ይዋጣላን ማለት እንደሀገር ዋጋ አስከፍሎናል። በዚህም መንገድ ለዘመናት ተጉዘን ያተረፍነው ድህነትን፤ ኋላቀርነትና ዕልቂትን ብቻ ነው።

የታሪካችን አንዱ ክፋይ ሆኖ ዘመናትን የተሻገረውን ጦርነትና ግጭትን ለማስወገድና የተረጋጋች፤ ሰላሟ የተጠበቀ እና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመጭው ትውልድ ለማውረስ ሀገራዊ ምክክሩ ይዞ የመጣውን ዕድል ልንጠቀምበት ይገባል።

> " ኢትዮጵያ ከፊቷ የተጋረጡ በርካታ ችግሮች ያሉባት አገር ናት፡፡ የአገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ጊዜ መስጠት አለባቸው፡፡ ጽንፍ ለጽንፍ ሆኖ ቃላት መወራወርና ይዋጣልን ማለት እንደሀገር ዋጋ አስከፍሉናል፡፡ በዚህም መንገድ ለዘመናት ተጉዘን ያተረፍነው ድህነትን፤ ኋላቀርነትና ዕልቂትን ብቻ ነው "

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ



# በሰው ሠራሽ አስተውሎት- የኢትዮጵያን ቋንቋዎች ለመማር

**ወርቅነሽ ደምሰው**

አሁን ባለንበት ዘመን በቴክኖሎጂ የረቀቀ የሰው ሠራሽ አስተውሎት (Artificial intelligence) በመጠቀም የሰው ልጆችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ቀላል የሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ እየዋሉ ይገኛሉ። በዚያ ልክ ቴክኖሎጂዎችን በመለማመድ በፍጥነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ከዘመኑ ጋር አብሮ ለመራመድ ጥረት የማድረጉ ስራም ተጠናክሮ ቀጥሏል። ይህም ሰዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ከቴክኖሎጂ ጋር ያላቸው ቁርኝት እንዲጨምርና እንዲያድግ እያደረገ ነው።

ለዚህም በእጃችን ላይ ያለውን ተንቀሳቃሽ ስልክ እንኳ ብንመለከት በቴክኖሎጂ አማካኝነት በቀላሉ ብዙ ጥቅሞች እያገኘን መሆኑን መገንዘብ ያስችለናል። ተንቀሳቃሽ ስልካችንን ተጠቅመን ምንም ነገር ሳይገድበን የምንፈልገውን መረጃና አገልግሎት በፍጥነት እያገኘን ነው። የጊዜና የጉልበት ብክነትን እያስቀረን፣ ካልተገባ ወጪ እየዳንን ነው፤ ባለንበት ቦታ ሆነን የምንፈልገውን መረጃም ሆነ አገልግሎት እንደልብ እንድናገኝ ቴክኖሎጂው አስችሎናል ማለት ይቻላል። ለምሳሌ የታክሲ አገልግሎት ፈልገን የታክሲ አገልግሎት የምናገኝበትን መተግበሪያ አውርደን ስናዝ የሚፈልገውን ታክሲ ያለበትን ቦታ፣ ወደኛ ሲመጣ ያለውን ሂደት፣ በስንት ሰዓት ውስጥ መድረስ እንደሚችል፤ ስለምንሄድበት መንገድ የትራፊክ ፍሰትና ሌሎች የተሟላና የተጠናከረ መረጃ በመስጠት እያገለገለ ይገኛል።

አሁን ደግሞ እየረቀቀ በመጣው ቴክኖሎጂ በሰው ሠራሽ አስተውሎት (Artificial intelligence) የተለያዩ አገልግሎቶችን ማግኘት እየተቻለ ነው። ቴክኖሎጂዎች እየረቀቁ ላቅ ወዳላ ደረጃ ለመድረሳቸው ብዙ ማሳያዎችን ማንሳት ይቻላል። በሰው ሠራሽ አስተውሎት ማሽን በማስተማር ማሽኑ ደግሞ መልሶ የሰው ልጅን እንዲያስተምር ማድረግ የተቻለበት ጊዜ ላይ ደርሰናል።

ከዚህ ግሩም ቴክኖሎጂ ግኝቶች መካከል እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2016 ኢትዮጵያውያን ጨምሮ ከተለያዩ ሀገራት በተውጣጡ የኮምፒውተር ሳይንስ ባለሙያዎች እንደተፈጠረች የሚነገርላት ‹‹ሶፊያ›› የተሰኘ መጠሪያ የተሰጣት ሮቦት ትጠቀሳለች። ‹‹ሶፊያ›› ሮቦት አስደናቂ ነገሮችን ስትፈጽም ተመልክተን ተደንቀናል። አብዛኞዎቻችን ይህንን ስናይ በሰው ልጆች የሰለጠነ ማሽን እንዲህ አይነት አስገራሚና አስደናቂ ሥራዎች ሲፈጸም እንዴት ብለን በእጅጉ ተገርመናል።

አሁን ደግሞ የሰው ልጅ የሚግባባበትን ቋንቋ ለማሽን በማስተማር ማሽኑ ቋንቋውን መልሶ እንዲያስተምር እየተደረገ ያለበት ሂደት ላይ ደርሰናል። ይህ ቋንቋን የማሽን ለማድረግ የሚካሄድ ሥርዓት ናቹራል ለርኒንግ ፕሮሰስ (natural language processing) ይሰኛል። በዚህ ዘዴ ቋንቋን ለማሽን በማስተማር ከተለያዩ ቁሶች፣ መተግበሪያዎችና ሶፍትዌሮች ጋር እንዲናበብ የሚያደርጉ ማስተማሪያ የሆኑ በርካታ የ‹‹ናቹራል ለርኒንግ›› አይነቶች እንዳሉ መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ።

በቅርቡም በኢትዮጵያ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ቋንቋ ማስተማር የሚችል የማሽን ሥርዓት ተሰርቶ ማጠናቀቁን ይፋ ማድረጉ ይታወሳል። የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ተስፋዬ ዘውዴ ኢንስቲትዩቱ የኢትዮጵያ የቋንቋዎች መማሪያ ሥርዓትን የያዘ መተግበሪያ ተግባራዊ ማድረጉን ይናገራሉ። እሳቸው እንደሚሉት፤ ይህ ሥርዓት የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች መማሪያ ነው። ሥርዓቱም ለሁለት ነገሮች ያገለግላል፤ ቋንቋዎችን ለመማር እና ድምጽን ወደ ጽሑፍ ለመቀየር የሚያስችል ነው።

ቋንቋዎችን ለመማር የሚያስችለው ሥርዓት የአማርኛ፣ የአፋን ኦሮሞ፣ የሱማሊኛና የትግረኛ ቋንቋዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ንግግርን፣ ሰላምታን፣ ቁጥሮችን፣ ቀናትን፣ ወራትን፣ ጊዜን፣ ወቅቶችን እና እነዚህን የመሳሳሉትን ነገሮች ለመለዋወጥና ለመማር ያግዛል።

ሁለተኛው ድምጽን ወደ ጽሑፍ መቀየሪያ ሥርዓት ነው፤ ይህ ደግሞ መጀመሪያ ሰዎች እየተነጋገሩ ያሉትን መተግበሪያ ላይ በአማርኛና በአፋን ኦሮሞ ቋንቋዎች መቅዳት የሚያስችል ሲሆን፤ ድምጹ ከተቀዳ በኋላ ትራንስክራይብ አድርግ ብለን ማሽኑን ስናዘው ድምጹን ወደ ጽሁፍ ይቀይራል። ከዚህ በተጨማሪም ቀደም ሲል የተቀረጸ ድምጽ ካለ የድምጽን ፋይል ወደዚህ መተግበሪያ በመጫን አስገብተን ወደ ምንፈልገው ጽሑፍ መለወጥ (መቀየር) የሚያስችለን ሥርዓት (ሲስተም) ነው።

ይህ ሥርዓት በዋናነት ለተለያዩ ተቋማት አገልግሎት መስጠት ያስችላል። ለምሳሌ በተለይ ለሚዲያ ተቋማት ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ድምጾች ከተቀረጹ በኋላ ወዲያውን ተጭኖ ወደ ሚፈለገው አይነት ጽሑፍ ተቀይሮ መልዕክቱን ማስተላለፍ ሲፈልጉ ይጠቀሙበታል። በትላልቅ ጉባኤዎች እና ስብሰባዎች ላይ የተደረጉ ውይይቶችን ድምጽ ከተቀረጸ በኋላ እንዲሁ በሁለቱ ቋንቋዎች (በአማርኛና በአፋን ኦሮሞ) ተጠቅሞ ወደ ጽሁፍ ቀይሮ ለመያዝ ያገለግለናል።

የኢትዮጵያ አርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ቋንቋዎችን ለመማር ትኩረት አድርጎ የሰራው በአራቱ ቋንቋዎች ላይ ነው የሚሉት አቶ ተስፋዬ፤ እስካሁን ባለው ሂደት እነዚህን ቋንቋዎች ማሽኑ እንዲማር ሲደረግ መቆየቱን ይናገራሉ። ማሽኑ የተማረውን መልሶ ለሰው ልጅ ችግር ፈቺ የሆነ አገልግሎቶች መስጠት መቻል አለበት በሚለው እሳቤ መሠረት አራት ቋንቋዎችን እንዲማር ተደርጓል። ይህም አንድ ሰው ከእነዚህ አራት ቋንቋዎች የማይችለውን ቋንቋ ለመማር ከፈለገ እንዲማር እድሉን ይከፍትለታል። ለምሳሌ አንድ ሶማሊኛ ቋንቋን የማይችል ሰው በሶማሊኛ ቋንቋ ሰላምታ ለመስጠት ከፈለገ በቋንቋው ሰላምታ ለመጠየቅ ምን ይባላል የሚለውን ለማወቅ ማሽኑን ሲጠይቅ ሶማሊኛ ቋንቋ የሚባለው በድምጽም በጽሑፍም ይሰጠዋል። በዚህም በአማርኛ ‹‹ሰላም›› የሚለውን ቃል በሶማሊኛም ‹‹እነበድ›› በሚል በጽምጹ እያደመጥን እንዲሁም በጽሁፍም እያየን ቋንቋውን እንድንማር ያስችላል ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም እንደምን ዋልክ፣ እንደምን ዋልሽ የሚሉትን እና የመሳሳሉትን ሌሎችንም አስፈላጊ የሆኑ መግባቢያዎችንም እንዲሁ በድምጽም በጽሁፍም መማር እንችላለን። ማንበብ ለማይችልም ሰው ድምጹን እየሰማ እንዲማር ይረዳዋል። ‹‹ቋንቋ ስንማር አስፈላጊ የሆኑ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ ያሉ ክህሎቶች ተጠቅመን እንድንማር ያስችለናል። በሰው ልጆች በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ለመግባባት ሊያግዙ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸውን ቋንቋዎች ቃላትን በማሽን ታግዘን እንድንማር የሚረዳ ነው›› ሲሉ ያብራራሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ መተግበሪያው በፕሌስቶር (play store) ላይ ከተጫነ ሦስት ወራት በላይ አስቆጥሯል። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ 3ሺ ያህል ሰዎች መተግበሪያውን አውርደው በመጫን እየተጠቀሙበት ነው። ነገር ግን ብዙ ሰዎች እንዲጠቀሙበት ለማድረግ በስፋት የማስተዋወቅ ሥራ መስራት አለበት።

ይህን መተግበሪያ ለመጠቀም የሚፈልጉ ሰዎች የአንድሮይድ (Androied) ተጠቃሚዎች ሆነው ዘመናዊ ስልክ ካላቸው ከፕሌስቶር (play store) ላይ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች መማር (learn Ethiopian language) የሚለውን መተግበሪያ በመፈለግ በስልካቸው ላይ በሚጫኑበት ጊዜ ሁለቱን አገልግሎቶች ያገኛሉ። አንደኛው ቋንቋው የሚያስተምራቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የተናገሩት ወይም በፋይል ያለን ድምጽ ወደ ጽሁፍ የሚቀየርላቸውን አገልግሎት በአንድ ላይ ማግኘት ያስችላቸዋል።

ይህን መተግበሪያ የሚጠቀሙ ቪፒኢን (VPN) አጥፍተው መጠቀም ይኖርባቸዋል። እስካሁን ባለው ሂደት በማንኛውም ሁኔታ ላይ በአንድሮይድ (Androied) ላይ ይሰራል። በቅርቡ ደግሞ የአፕል (Apple) ምርት የሆኑ ዘመናዊ ስልክ ተጠቃሚዎች አገልግሎቱን እንዲያገኙ ለማድረግ የሚሰሩ ሥራዎችን እየተጠናቀቁ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪም በዌብ ሳይት (wave based) እንዲሰራ ለማድረግ የሚሰሩ ሥራዎች እየተጠናቀቁ በመሆኑ በቅርቡ ይለቀቃሉ። በኮምፒዩተርም ሆነ በአይፎን (I Phone) ስልኮች መጠቀም የሚያስችለን ሥራ እየተጠናቀቀ ነው በማለት አቶ ተስፋዬ ያመላከቱት።

እስካሁን ድረስ ኢንስቲትዩቱ በተቻለው መጠን መተግበሪያውን በማስተዋወቅ ላይ ይገኛል የሚሉት አቶ ተስፋዬ፤ ነገር ግን በበቂ ሁኔታ የማስተዋወቅ ሥራ እየተሰራበት እንዳልሆነ ይናገራሉ። በቀጣይ መተግበሪያውን በማስተዋወቅ ረገድ የሀገራችን ሚዲያዎችም ሆነ ሌሎች አገልግሎቱን የሚጠቀሙ የተሻለ አገልግሎት እያገኙበት ያሉ ሰዎች በስፋት እንዲጠቀሙበት ለማድረግም ሆነ ሌሎችም እንዲጠቀሙበት ለማስቻል የማስተዋወቁ ሥራ በትኩረት ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

‹‹እንደ ኢንስቲትዩትም ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ትልቅ ሥራ ነው የተሰራው። የሀገራችንን ቋንቋዎች እንደዚህ ለማሽን አስተምሮ መልሶ ማሽን ለሰው ልጅ ትርጉም እንዲሰጥ ማድረግ ሥራ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰራ ነው። ባለፉት ጊዜያት ይህ ሥራ እንኳን ሊሞከር ሊታሰብ የማይችል ነበር›› የሚሉት አቶ ተስፋዬ፤ አሁን ላይ ግን በአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት እውን ሆኗል ይላሉ። ተቋሙ መተግበሪያውን ማስተዋወቅ ላይ ውስንነቶች እንዳሉም ተናግረዋል። በዚህ ረገድ ከሚዲያ ተቋማት፣ ከባለድርሻ አካላት፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ከምርምር ተቋማት ጋር በጋራ ውጤታማ ሥራ ለመስራት ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል ሲሉም ተናግረዋል።

ይህ መተግበሪያ በደንብ የተሰራ ዓለም አቀፍ ምልከታዎችን ያካተተ፣ ሳይንሳዊ ትንታኔዎች ታክሎበት የተሰራ ነው የሚሉት አቶ ተስፋዬ፤ አሁን ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የዚህን መተግበሪያ ጥቅሙን ሰው በደንብ መረዳትና መጠቀም መቻል እንዳለበት ይጠቁማሉ። በቀጣይ አጠቃቀም ላይ ያሉ ክፍተቶች ካሉ እየታዩ የሚሻሻሉበት ሁኔታ እንደሚኖር ያመላክታሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ የአርተፊሻል አንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ትኩረት አድርጎባቸው ከሚሰራባቸው ነገሮች አንዱ ለማሽን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር/ machine learn Ethiopian language /natural language processing/ በሚለው ክፍል ውስጥ በሀገረኛ ቋንቋዎች ላይ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል። በቅርቡ የተለያዩ የምርት አገልግሎቶች የሰው ሠራሽ አስተውሎት አቅም ያላቸውን ያዳበሩ ሲስተሞችን ለተጠቃሚው ሕዝብ ተደራሽ ለማድረስ ተቋሙ ዝግጅቱን አጠናቅቋል።

በጤና፣ በግብርና፣ በትምህርት፣ በትራንስፖርትና በሌሎች ዘርፎች ላይ የሰው ሠራሽ አስተውሎት ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው የሚለው አቶ ተስፋዬ፤ ኢንስቲትዩቱ እነዚህን ወደ ተጠቃሚው ተደራሽ ለማድረግና በተጨማሪም ለሚሰራቸው ሌሎች የምርምር ሥራዎች ማንኛውም ዘርፍ ላይ የሚገኙ ዳታዎችን (መረጃዎች) በመስጠት ባለድርሻ አካላት ትብብር ሊያደርጉ እንደሚገባ ይጠቁማሉ። አሁን ላይ እነዚህን ምርቶች ለማውጣት ዓመታት እየወሰደ ያለው ሥራ መሰራቱን አስታውሰው፣ ከዚያ ባጠረ ጊዜ ውስጥ በፍጥነት መፍትሔ መስጠት የሚያስችሉ ሥራዎች ሠርቶ ለማቅረብ ባለድርሻ አካላት መረጃን በማጋራት በኩል ትብብር ቢያደርጉ ሲሉም ጠይቀዋል። ይህም በሀገራችን የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት ይረዳል በማለት ተናግረዋል።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ ሰው ሠራሽ አስተውሎት የሰው ልጅ የሚግባባቸውን ቋንቋዎች ለማሽን በማስተማር የቋንቋውን አድማስ ለማስፋትና ጠቀሜታው እንዲያድግ በተደረገው ጥረት በርካታ ውጤቶች እየተመዘገቡ ይገኛሉ። በሀገራችን የሰው ሠራሽ አስተውሎት ሥራዎች በጅምር ላይ ያሉ ቢሆንም፣ የተሰሩ ሥራዎች ሊደነቁና ሊበረታቱ ይገባቸዋል። በቴክኖሎጂዎቹ ለመጠቀም ጥረት ማድረግም ያስፈልጋል።

ከቴክኖሎጂ ውጭ መሆን በማይቻልበት ጊዜ ላይ ባለንበት በዚህ ዲጅታል ዘመን ከዘመኑ ጋር መራመድ የግድ መሆኑን ጠቅሰዋል። በመሆኑም ሌሎች የሰሯቸውን ቴክኖሎጂዎች ከመጠቀም ባሻገር የራሳችን የምንላቸውን የሀገራችንን አውድና ነባራዊ ሁኔታ መሠረት አድርገው የሚሰሩ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ነገ የሚፈጠሩ አዲዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የራሱን አስተዋፅኦ እንደሚኖረው መገንዘብ ይገባል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ሌላኛው የኢትዮጵያ አረንጓዴ ወርቅ-እንሰት

ምሕረት ሞገስ

የእንሰት ተክል ከ1939 ዓ.ም ጀምሮ የተካሔዱ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፤ ጠቃሚነቱ ታውቆ በሺ ለሚቆጠሩ ዓመታት ለምግብነት ሲውል ቆይቷል። ይህ ተክል በብዛት ለሰው ልጆች ለምግብነት እና ለከብቶች መኖ፣ ለመድሃኒትነት እና ምንጣፍን ለመሳሰሉ የተለያዩ አገልግሎቶች መዋል ይችላል። ለአፈር እና ውሃ ጥበቃ የሚያበረክተው አስተዋፅኦም በጣም ከፍተኛ መሆኑ የተነገረለት ይኸው ተክል፤ ደጋ እና ወይናደጋ ብቻ ሳይሆን ቆላም ማደግ የሚችል መሆኑ በጥናት ተረጋግጧል።

የእንሰት ተክል ድርቅን በመቋቋም በኩልም ሰፊ አስተዋፅኦ አለው። እንሰት ለምግብነት እና ለቤት ውስጥ ለተለያዩ መገልገያዎች መጠቀሚያነት ለመዋል የሚደርስበት ጊዜ እንደሚተከልበት አካባቢ መለያየት እና እንደእንሰት ዝርያው ዓይነት ከሁለት ዓመት ተኩል እስከ ስምንት ዓመት ሊቆይ እንደሚችል የዘርፉ ተመራማሪዎች ይናገራሉ። በባህላዊ መንገድ ከመሬት ከተነሳ በኋላ ለምግብ ዝግጁ ለመሆን እስከ ሁለት ወር የሚፈጅ ሲሆን፤ አሁን ግን በምርምር የእንሰት ማብላያ በመዘጋጀቱ ከሰባት እስከ አስር ቀን ባለ ጊዜ ውስጥ ዝግጁ መሆን እንደሚችል በሳይንስ አረጋግጠናል የሚሉት አዲሱ ፍቃዱ (ዶ/ር) ናቸው።

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ እና የእንሰት ፕሮጀክቶች አስተባባሪው አዲሱ (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ እንሰት አንዴ ከተብላላ በኋላ ተሸፍኖ ከዓመት በላይ መቆየት ይችላል። ምርቱ በማንኛውም ወቅት ከመሬት መነሳት የሚችል እና በየትኛውም ወር በሚፈለግበት ጊዜ በቀላሉ ለምግብነት የሚውል ነው።

እንሰት ለምግብነት ሲውል ለሰውነት ከሚያስፈልጉ ንጥረ ነገሮች መካከል ተጠቃሽ የሆኑትን፤ ፋይበር እና ካርቦ ሃይድሬት የመሳሰሉትን እንደያዘ የሚያስረዱት ደግሞ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር ዮሐንስ ገብሩ (ዶ/ር) ናቸው።

እንሰት በኢትዮጵያ ብቻ በቀድሞ አጠራሩ በደቡብ ክልል በስፋት ለምግብነት የሚውል ሲሆን፤ በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎችም የሚገኝ ተክል ነው። ለረዥም ጊዜ ውሃ ሳያገኝ መቆየት የሚችለው ይኸው ተክል፤ በ1977 ዓ.ም በኢትዮጵያ ተከስቶ በነበረው ድርቅ እንሰት አብቃይ አካባቢዎች ያለመጠቃታቸው ምክንያት ይኸው መሆኑን ዮሐንስ (ዶ/ር) አስረድተዋል።

አዲሱ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለፁት፤ ድርቅን በመቋቋም እና የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ሰፊ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት በጥናት ማመላከት ተችሏል። እስከ አሁን በተካሔደው ጥናት በአንድ ቦታ ላይ ለሶስት ዓመት ሳይቋረጥ ስንዴ ሲተከል ከእንሰቱ የሚገኘው ምርት የስንዴውን እጥፍ መሆኑን ማወቅ ተችሏል።

በደቡብ በተለይም በጉራጌ አካባቢ ሴቶች ሞያቸው የሚለካው እንሰትን ለብዙ ጊዜ በጉድጓድ ውስጥ በማስቀመጥ ነው። ነገር ግን ከመሬት ተነስቶ ከተዘጋጀ በኋላ ለምግብነት ከመዋሉ በፊት ለዓመታት ጉድጓድ ውስጥ ተከማችቶ እና ተሸፍኖ መቆየቱ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፤ ለቆጮ ተመጋቢ ሰዎች ጠዓሙ ቢጨምርም፤ የምግብ ይዘቱ ይቀንሳል ብለዋል። በሌላ በኩል ሲቆይ የተለየ ሽታ የሚያመጣ ሲሆን፤ የምግብ ይዘቱን እንዳይቀንስ እና ሽታውን ለማሻሻል ጥናቶች በመካሔድ ላይ መሆናቸውን ዮሐንስ (ዶ/ር) ተናግረዋል።

እንሰት በፊት በነበረው የቤት ቆጠራ ዋነኛ የምግብነት ተጠቃሚ ቁጥር 20 ሚሊየን ይደርሳል ተባለ እንጂ፤ ከምርታማነቱ አንፃር አሁን ላይ የእንሰት ተመጋቢው ቁጥር ከ30 ሚሊየን የሚያንስ አለመሆኑን አዲሱ (ዶ/ር) ተናግረዋል።

እንደ አዲሱ (ዶ/ር) ገለፃ፤ እንሰት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ያስችላል የተባለባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ድርቅን የመቋቋም ዝንባሌ አለው ያሰኘውም እንሰት በቀላሉ ውሃን የሚይዝ በመሆኑ፤ ለአንድ ብቻ ሳይሆን ለሁለት ዓመት ዝናብ ባይኖርም ሌሎች የምግብ ሰብሎች ስንዴ፣ ጤፍና በቆሎን የመሳሰሉ የሰብል እህሎች ማምረት ባይቻልም እንሰት ሳይጠወልግ ቆይቶ በቀላሉ በማንኛውም ጊዜ ለምግብነት መዋል ስለሚችል ነው።

በሌላ በኩል ከምርታማነት አንፃርም እስከ አሁን በተካሔደው ጥናት በአንድ ቦታ ላይ ለሶስት ዓመት ሳይቋረጥ ስንዴ ሲተከል ከእንሰቱ የሚገኘው ምርት የስንዴውን እጥፍ መሆኑን ማወቅ ተችሏል። በተጨማሪ እንሰት በተተከለበት በትንሽ ቦታ ብዙ ምርት ማግኘት ከመቻሉም ባሻገር፤ እንደሌሎች ሰብሎች ምርቱ የሚሰበሰብበት ወቅት የተወሰነ አይደለም። መስከረምም ሆነ ነሐሴ ጥቅምትም ሆነ ሕዳር በማንኛውም ጊዜ እንሰትን ለምግብነት ማዋል ይቻላል ሲሉ አዲሱ (ዶ/ር) ተናግረዋል።

እንሰት ላይ ያለው ችግር አጠውልግ የሚባል በሽታ ነው። ከአጠውልግ በተጨማሪ እንሰትን የሚቦረቡሩ ጥቃቅን ነፍሳቶችም አሉ። እነዚህ እንሰት ላይ የተጋረጡ ፈተናዎችን ለመከላከል ብዙ ምርምሮች የተካሔዱ ሲሆን፤ በተለይ የበሽታው መንስኤ እና የመከላከያው መንገድ ምንድን ነው በሚል ጥናቶች በመካሔድ ላይ ናቸው ብለዋል።

በጥናት ንፁህ፣ ከበሽታ እና ከተባይ የፀዳ የእንሰት ችግኝ ለአርሶ አደር የሚያቀርብ የችግኝ ምንጭ አለመኖሩ፤ በተለመደው መንገድ አርሶ አደሮች ችግኙን የሚሻሻጡበት ሁኔታ መኖሩ ለበሽታው መስፋፋት በመንስኤነት የተቀመጠ ሲሆን፤ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በከፍተኛ መጠን ችግኞችን በማባዛት ለማሰራጨት ጥረት እያደረግን መሆኑን አዲሱ (ዶ/ር) አመላክተዋል።

ሌላኛው በአዲሱ (ዶ/ር) የተገለፀው ችግር እንሰት የሚዘጋጅበት መንገድ አድካሚነትን የተመለከተው ጉዳይ ነው። ሲዳማ፣ ጌዶዮም ሆነ ጉራጌ በየትኛውም አካባቢ ያሉ ሰዎች እንሰትን የሚፍቁት አድካሚ በሆነ መልኩ በባህላዊ መንገድ በእንጨት፣ በአጥንት እና በቀርከሃ ነው። በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ አዳዲስ መፋቂያዎችን በማዘጋጀት እና አርሶ አደር ጋር ደርሶ በመሞከር በመጨረሻም አርሶ አደሩ ምቹ ነው የሚለውን በማባዛት እየተጠቀሙበት ነው። ነገር ግን እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ከባድ ችግር ቢያቃልሉም፤ አባዝቶ ለአብዛኞቹ ተጠቃሚዎች የማድረስ ችግር አለ።

አዲሱ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ለእንሰት አንድ ዶላር አይወጣም። እንሰት አምራች አርሶ አደር የግብርና ባለሞያም ሆነ ማዳበሪያ አይጠቀምም። ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ እንሰት ሌላኛው አረንጓዴ ወርቅ መሆኑን የመገንዘብ ችግር አለ። እያዳንዳቸው ከ30 እና 40 በላይ እስከ 200 እንሰት ያላቸው አርሶ አደሮች አሉ። ይህ እንሰት የአገር ሃብት ነው። ለዓመታት ከሚቆይ ተፍቆ ለምግብነት ቢውል እና በእርሱ ቦታ ሌላ ቢተከል እጅግ ብዙ ጥቅም ማግኘት ይቻላል። በዘመናዊ መንገድ ተመርቶ ለአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለውጪ ገበያ ቢቀርብ፤ የውጭ ምንዛሪን ያስገኛል። ነገር ግን በእንሰት አብቃይ አካባቢዎች እንሰት ቦታ ይዞ ወደ ምግብነት ሳይቀየር እና ገበያ ላይ ሳይውል ከመቆየቱም በተጨማሪ፤ ከተፋቀ በኋላ ጉድጓድ ውስጥ ለረዥም ዓመት የመቅበር ባህል አለ። ይህ አንዳንዴ ኀርፍ ገብቶ ምርቱ የሚጠቁርበት እና ሙሉ ለሙሉ የሚበላሽበት ሁኔታ መኖሩንም አዲሱ (ዶ/ር) ተናግረዋል።

ጉድጓድ ውስጥ ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን፤ በሌላ በኩል አንድ አርሶ አደር ከ100 እንሰት ውስጥ 5ቱን ለምግብነት አውሎ 95ቱን የደረሰ እንሰትን አራት እና አምስት ዓመት ማስቀመጡ በተመሳሳይ አርሶ አደሩንም ሆነ አገርን ማክሰር ነው። ተፍቆ ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ ለብዙ ዓመታት ቢቀመጥም ኪሳራ ነው። ነገር ግን ምግቡ ለሰው ልጅ ውሎ ሌላ ቢዘጋጅ የተሻለ ነው። አንደኛ አርሶ አደሩ ለራሱ ተጨማሪ ገቢ ያገኛል፤ ሌሎችም በተመጣጣኝ ዋጋ ይመገባሉ ብለዋል።

ከኢኮኖሚ እና የምግብ ይዘትን ከመቀነስ አንፃርም ጉድጓድ ውስጥ ባይቀመጥ ይሻላል ያሉት አዲሱ (ዶ/ር)፤ ቀድሞ ከውጪ የሚገባውን ስንዴ በአገር ውስጥ ተተክቷል። አሁን ደግሞ በስፋት ማዳበሪያ እየገባ ነው። የማዳበሪያ ወጪንም ለመቀነስ እንሰት ላይ ቢሠራ ትልቅ ጥቅም ማግኘት ይቻላል ብለዋል።

እንደ አዲሱ (ዶ/ር) ገለፃ፤ እንሰት በአገር ውስጥ የማዳበሪያ ወጪንም ሆነ ከውጪ የሚገቡ ለምግብነት የሚውሉ ምግቦችን፣ የውጭ ምንዛሪ ወጪን እና የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ የሚኖረው ጠቀሜታ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። ነገር ግን እንሰትን በዚህ መልኩ በመረዳት በኩል ሰፊ ክፍተት መኖሩን አብራርተዋል።

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ እንሰት ከጉድጓድ ይውጣ የሚል ዘመቻ በማካሔድ እና እንሰትን ለማብላያነት የሚያገለግል እና ማስቀመጫ የሚሆን ዕቃ በማዘጋጀት የማስተዋወቅ ሥራ እየሠራ መሆኑንም ተናግረዋል። ይህንን ዩኒቨርሲቲው ቢሠራም፤ በተለይ ወደ ደቡብ ምዕራብ ወደ ሃድያ ዕቃውን የማስተዋወቅ እና የማስፋፋት



ሥራ አለመሰራቱ እና የተጠቃሚውን ቁጥር በሰፊው መጨመር አለመቻሉ ሌላኛው ችግር ነው ብለዋል።

በተመሳሳይ ዮሐንስ (ዶ/ር) የተገለፀው ችግር አጠውልግ የሚባል የእንሰት በሽታ ሲሆን፤ ሌላኛው ምግቡን ለማዘጋጀት አድካሚ መሆኑን ነው። በተለምዶ አጠውልግ የሚባለው በሽታ ባክቴሪያ ሲሆን፤ ለመድሃኒትነት የሚውሉትን የተመረጡ የእንሰት ዝርያዎችን እያጠፋ መሆኑን አብራርተዋል። እንሰትን ለምግብነት ለማዋል ሴቶች እግራቸውን ሰቅለው ለረዥም ሰዓት ሲፍቁ መዋላቸው በጣም እየጎዳቸው መሆኑንም ተናግረዋል። ይህን ተከትሎ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ሁለቱ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ እየሠራ መሆኑንም አስረድተዋል።

እንደ ዮሐንስ (ዶ/ር) ገለፃ፤ ወደፊት ሁለቱን ነገሮች መከላከል ካልተቻለ እንሰት ሊታጣ የሚችልበት አደጋ ያጋጥማል። ይህንን ለመከላከል ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የእንሰት ዘሮች ማባዣ እና ማቆያ ጣቢያ አዘጋጅቷል። በጣቢያቸው ሊጠፉ የደረሱትን ጠብቀው ይዘዋል። ከመያዝ ባሻገር እስከ 2014 ዓ.ም ዝርያዎቹን መልሰው ለሕብረተሰቡ ሲያሰራጩ ቆይተዋል።

በተጨማሪ ጥናት በማካሔድ ችግኝ በሚጓጓዝበት ጊዜ ባክቴሪያዎቹ ካሉበት አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ የማስፋፋት ሁኔታዎች መኖራቸውን አውቀዋል። ይህን ተከትሎ ባክቴሪያዎቹ የሚስፋፋባቸውን የተለያዩ መንገዶችን ለሕብረተሰቡ ስልጠና እየሠጡ መሆኑንም ተናግረዋል።

አዲሱ (ዶ/ር) ሲናገሩ፤ እንሰት ቢያንስ አንድ አራተኛው የአገሪቱን ሕዝብ የያዘ ነው። የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ያለው ሚና በጣም ከፍተኛ ነው። በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የእንሰት ምርት ውስጥ ሩብ የሚሆነው እንኳ ጥቅም ላይ አልዋለም። ውስን ሥራዎች በትኩረት ቢሠሩም፤ በተመጣጣኝ ዋጋ የእንሰት ምግብን በቀላሉ ለገበያ የሚውልበት እና ብዙዎች የሥራ ዕድል የሚያገኙበት ዕድልን መፍጠር ይቻላል ሲሉ ወደፊት መሆን ያለበትን አመላክተዋል።

እንሰት ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ለምግብነት የሚውል በመሆኑ፤ ለምግብ ቱሪዝም ማዋልም ይቻላል። ያሉት ዶክተር አዲሱ፤ ምንም ዓይነት ኬሚካል የማይነካው፤ ያልተዳቀለ ጤናማ ምግብ ሲሆን፤ የማስተዋወቅ ሥራ ቢሠራ በዓለም ደረጃ ገበያ ላይ በመሳተፍ ከምግብ ቱሪዝም በተጨማሪ በውጪ የእንሰት ምርት ሽያጭ ብዙ ማግኘት ይቻላል ብለዋል።

ዮሐንስ (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ በዩኒቨርስቲያቸው በኩል ባህላዊ የእንሰት ምግብ አመራረት ዘዴን ለማዘመን በመስራት ላይ ይገኛሉ። ማህበረሰቡ እንዲጠቀምበት ማድረግ እና ከእንሰት የተለያዩ ምግቦችን የማስተዋወቅ ሥራን በማከናወን ላይ ናቸው። አርሶ አደሮቹም ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ጥሩ ምርት በማምረት ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ ለወጣቶች የሥራ ዕድል እየተፈጠረበት ነው ማለት ይቻላል።

ዮሐንስ (ዶ/ር) የእንሰት አጠውልግ በሽታ በጣም ረዥም ጊዜ የቆየ መሆኑን አስታውሰው፤ በእነርሱ ዩኒቨርሲቲም ወደፊት በሽታውን የሚቋቋሙ ዝርያዎችን መፈለግ አንደኛው ሥራቸው አድርገው በመስራት ላይ የሚገኙ መሆኑን ተናግረዋል። በሽታውን የሚያጠፋ መድሃኒት በመፈለግ ላይ መሆናቸውን ጠቁመው፤ የመድሃኒት ፍለጋው በዘመናዊ መልኩ ብቻ ሳይሆን፤ ህብረተሰቡ በባህላዊ ዕውቀቱ ለረዥም ጊዜ በሽታውን ሲከላከል የቆየበትን መንገድም እያዩ መሆኑን ተናግረዋል።

ይህን በሽታ ለማጥፋት ያልተቻለው ህብረተሰቡ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ባህላዊ መድሃኒቱን ተጠቅሞ፤ ሌሎች ቦታዎች ላይ ሳይጠቀም ሲቀር የተስፋፋ ነው የሚል መላምት ተይዞ ጥናት እየተካሔደ ነው ብለዋል።

እንሰት እየፋቁ የሚደክሙ ሴቶች ድካማቸውን ለመቀነስ ዘመናዊውን ማሽን ወደ ገበያው ማስገባት እና በማሽን እንዲያመርቱ ማድረግ ላይ ወደፊት በስፋት መሰራት እንዳለበት አመልክተው፤ በዚህ ላይ ዩኒቨርሲቲው ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተቋሞችም አተኩረው መሥራት አለባቸው ብለዋል። ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ሁለት የናሙና ማሽኖችን ፕሮቶታይፕ ለመስራት ጨርሷል። አንደኛው ረዥም ጊዜ የቆየ ሲሆን፤ ሁለተኛው ግን ከአንድ ዓለም አቀፍ ኢንሼቲቭ ጋር በመተባበር፤ ማሽኖቹን አምርተው ለማስፋፋት ዝግጅታቸውን እንደጨረሱ ተናግረዋል።

በመጨረሻም ወደ ፊት ሥራውን በመሥራት ማሳ ላይ በስፋት ያሉትን እንሰቶች ለምግብነት ለማዋል ማሽኑን በፍጥነት ወደ ሥራ የማስገባት ዕቅድ ይዘው በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸውን አመልክተው፤ በሽታው ላይም ጥልቅ ምርምር ለመሥራት ማቀዳቸውን ተናግረዋል።

እንደ ምሁራኑ ገለፃ፤ በአጠቃላይ እንሰት እጅግ ጠቃሚ ነገር ግን ተገቢውን ትኩረት ያልተሰጠው ተክል ነው። ይህንን ተክል የተደቀነበትን የአጠውልግ በሽታ መከላከል እና የአዘገጃጀት ሁኔታውን ቀለል ማድረግ ካልተቻለ በተመጋቢው ላይ የሚፈጥረው ችግር ከፍተኛ ሲሆን፤ በተክሉ ላይ ትኩረት ሰጥቶ ከተሠራ ግን ድርቅ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ፤ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፤ ከምግብ ቱሪዝም ተጠቃሚ ለመሆን እና የተክሉን ምርት ለውጪ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪን ለማግኘት ያስችላል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# በበጎ ምግባሯ ለብዙዎች የደረሰች እንስት

**ሰሚራ በርሀ**

የቲአትር ባለሙያ ናት። በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ውስጥም ሠርታለች። በአሁኑ ጊዜም በአሜሪካን ሀገር ነው የምትኖረው። ኑሮም ሆነ የሥራ ጫና ሳያግዳት በማህበራዊ ድህረ - ገጽ ላይ በርካታ የበጎ አድራጎት ሥራ በማከናወን ላይ ትገኛለች። ሌሎች ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር እያከናወነች ባለው የበጎ አድራጎት ሥራዎቿ ተፅዕኖ ፈጣሪ ለመሆን ችላለች።በዚህ መልካም ሥራ ላይ የምትገኘውን ሕይወት ታደሰን ስለሕይወት ልምዷ እንድታካፍለን፣ስለበጎ ሥራዎችዋም እንድታጫውተን በመጋበዝ ቆይታ አድርገናል።

ሕይወት ትምህርቷን የተከታተለችው ተወልዳ ባደገችበት ጎንደር ከተማ ውስጥ ነው።ሕይወት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን የተከታተለችበት ፃድቁ ዮሃንስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ኢትዮጵያን በተለያየ መንገድ ያስጠሩ ታላላቅ ሰዎችን ያፈራ መሆኑንና የፊልም ባለሙያውን ፕሮፌሰር ሀይሌ ገሪማን ለአብነት ትጠቅሳለች።

ሕይወት ስለትምህርትቤት ቆይታዋም እንደነገረችን፤ ከልጅነቷ ጀምሮ የማንበብ ልምድ ስለነበራት ትምህርት ቤት ውስጥ በተለያዩ ክበቦች ውስጥ በንቃት ትሳተፍ ነበር።

ሕይወት ትምህርቷም ሆነ ኑሮዋ በተወለደችበት ጎንደር ከተማ አልዘለቀም። አያቷ እማሆይ የሺ ተሰማ በማረፋቸው ምክንያት ወደ አዲስ አበባ ከተማ ለመምጣት ተገደደች።አዲስ አበባ ከተማ በአክስቷ ቤት ሆና የመሰናዶ ትምህርቷን ቀጠለች።

ሕይወት የልጅነት ፍላጎቷ እና ተሰጥኦዋ አብሯት አድጎ ፤ ከተማን ተሻግሮ ወደ ቲአትር ሙያ እንድታዘነብል አድርጓታል። የመሰናዶ ትምህርቷን ስትጨርስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቲአትር እና ሥነ-ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀላቀለች ። የዩኒቨርሲቲ ተመርቃ እንደወጣችም በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ውስጥ የመሥራት እድሉን አግኝታለች። ‹‹ራሴን እንደ ቲአትር ባለሙያ እንጂ እንደጋዜጠኛ አልቆጥረውም ይህ ማዕረግ ይገባኛል ብዬም አላስብም። ነገር ግን ቲአትር እና ሚዲያው በሀገራችን የተቀራረበ ነገር በመሆኑ የመገናኛ ብዙሃን ላይ የመሥራት እድሉ ነበረኝ በዚህም በጣም ደስተኛ ነኝ። እኔም በዚህ ሙያ ላይ ጋዜጠኝነትን ተምረውና ብዙ ዋጋ ከፍለው የሚሠሩበት የማደንቃቸው ጋዜጠኞች አሉ›› ስትልም ትገልጻለች።

‹‹በምድር ላይ ስኖር በልቼ ፣ ጥሩ ለብሼ ፣ አልያም ጥሩ መኪና ይዤ ብቻ ለመኖር ተፈጥሪያለሁ ብዬ አላስብም ነገር ግን የቅርቤ ከምላቸው ሰዎች ባለፈ ለማላውቃቸው እነሱም ለማያውቁኝ ለተቸገሩ ርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ ለነርሱ መድረስ እፈልጋለሁ። ሰዎችን በማገዝ መማር እየፈለጉ ካልቻሉት ጋር ፣ መኖር እየፈለጉ ከከበዳቸው ጋር ችግራቸውን እየተጋራሁ መኖር የምንጊዜም ፍላጎቴ ነው።›› የምትለው ሕይወት ሙያዋን ለበጎ ምግባር በማዋልም ተጠቅማበታለች።

ሕይወት የግልዋን የማህበራዊ ገፅ በጎ ሥራዎችን ለመሥራትና መልካም መልዕክቶችን ሃሳቦችን ለማስተላለፍ ትጠቀምበታለች። ማህበራዊ ሚዲያን አብዝታ መጠቀም እና ጊዜዋን ለበጎ ዓላማ መስጠት የጀመረችውም ኮቪድ 19 ቫይረስ ወረሽሽኝ በዓለም ላይ ስጋት መሆኑ ይፋ በተደረገበት ወቅት ብዙዎች በቤታቸው መቆየት ተገደው በነበረበት ወቅት ነው።

አሜሪካ ኮቪድ አብዝቶ ከመታቸው ሀገራት አንዷ ነበረች በዚህ ጊዜም ሕይወት ሥራዋን አቁማ በቤት ውስጥ መቀመት ነበረባት። ወቅቱ ምንም እንኳን ለኢኮኖሚ መዳከም ምክንያት የሆነ እና የብዙዎችን ሕይወት ችግር ውስጥ የከተተ ቢሆንም እጅግ በጣም ብዙ አዳዲስ ሃሳቦች የተፈጠሩበት እና ሰዎች ራሳቸውን እንዲፈትሹበት እድል የሰጠ እንደነበር አይዘነጋም። ሕይወትም በቤቷ ስትቆይ በቤት ውስጥ ከሚኖርባት ሃላፊነት ባሻገር ሰፊ ሰዓቷን የማህበራዊ ገፅ ላይ ማሳለፍ ጀመረች። በማህበራዊ ገፅ ላይም ሌሎች ቤተሰቦችን አፈራች።

ወደ በጎ አድራጎት ሥራዎች እንድትገባ መነሻ የሆናት ግን በኢትዮጵያ የሚገኘው የመቄዶኒያ የአረጋውያን መርጃ ማዕከል በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት ማዕከሉን ለመጎብኘት የሚሄዱ እንግዶች ቁጥር እጅግ በጣም በመቀነሱ በማዕከሉ ለሚገኙ አረጋውያንና ራሳቸውን መንከባከብ ለማይችሉ አዋቂዎች የዳይፐር እጥረት እንደገጠመው በመስማቷ ነው። እርስዋም በምትኖርበት ሀገር በቀላሉ ማግኘት ስለምትችል የቅርቧ የሆኑትን ሰዎች በማስተባበር ያሰባሰበችውን ዳይፐር በቨርጂኒያ ከተማ ለሚገኘው የመቄዶኒያ ተወካይ በመስጠት ማድረስ ቻለች።

በዚህ መነሻም በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በንቃት በመሳተፍ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን መሥራቷን አጠናክራ ቀጠለች። በማህበራዊ ገፅ ላይም የተለያዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች ታሪክ ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ ሌሎች ተከታዮቿም ሆኑ ሃሳቧን የሚደግፉ ሰዎች እንዲሳተፉበት ታደርጋለች። ሕይወት በምታጋራቸው ታሪኮች በተለያየ ምክንያት ኑሯቸው የከበዳቸው ከባድ የሕይወት ውጣውረድን ያሳለፉ ፤ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ምክንያት ታክመው ለመዳን ከፍተኛ የህክምና ወጪ ተጠይቀው የሌሎችን ርዳታ የሚፈልጉ ህፃናት እና አዋቂዎች ጭምር ናቸው።

በዚህ መልኩ የምታከናውነው የበጎ ሥራዋ የሰዎችን እምነት ከማግኘት ባሻገር የምትኖርበት አሜሪካ ሀገር እያንዳንዱ ሰዓት ገንዘብ የሆነበት ሀገር በመሆኑ ከሥራ ከግል ሕይወት የተቀነሰ ሰዓት ለዚህ ዓላማ መስዋዕት ማድረግን ይጠይቃል። ነገር ግን በሕይወት አገላለፅ ከሰው ሕይወት ጋር አልያም ለህፃናት ከማድረስ ጋር ሲነፃፀር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም ትላለች።

ሕይወት በምታደርጋቸው የበጎ አድራጎት ሥራዎችና ቅስቀሳዎች ላይ በአብዛኛው በገንዘብ እጥረት ምክንያት መታከም ያልቻሉ የልብ ህመሙማን ህፃናትን በተመለከተ በማህበራዊ ድረገጿ ላይ በተደጋጋሚ ታጋራለች ። ‹‹ከልብ ህሙማን ህፃናት ጋር መሥራት የጀመረችበትን አጋጣሚም እንደገለጸችው የልብ ህሙማን ማዕከል አምባሳደር የሆነችው አርቲስት መሠረት መብራቴ ‹‹የገና ስጦታችሁን ለልብ ህሙማን ›› የሚል ማስታወቂያ ባየችበት ጊዜ ነው።

‹‹ጊዜው በኮቪድ ምክንያት ቤት ውስጥ የተቀመጥንበት ሰዓት ነበር እናም አንድ የልብ ህመም ያለበት እና ህክምና የሚያስፈልገው ሕፃን ልጅ በጊዜው ለመታከም የሚያስፈልገው ወደ 100 ሺህ ብር ነበር ፤ ይሄ ደግሞ እኔ በምኖርበት ሀገር ገንዘብ (በዶላር) ሲሰላ ያን ያህል የሚከብድ አልነበረም ፤ ስለዚህ በዚህ በዓል ቢያንስ አንድ ህፃን ማሳከም ብንችል ብዬ አሰብኩኝ ይሄንንም ሃሳቡን ለወዳጆቼ አካፈልኳቸው እነሱም ተስማሙ እናም በመጀመሪያ ርዳታችን 3 ልጅ መታከም የሚችልበትን ወደ 270 ሺህ ብር የሚጠጋ ገንዘብ መሰብሰብ ቻልን›› ስትልም ታስታውሳለች።

ሕይወት እንደገለጸችልን፤ አብዛኛውን ጊዜ በማህበራዊ ገፅ የምታጋራቸው እገዛ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች የሚገኙት በኢትዮጵያ ውስጥ ነው። እሷ ደግሞ የምትኖረው ከሀገር ርቃ ነው። ነገር ግን በሷ ቁርጠኝነት ፣ ደግ ልብና ጊዜው በደረሰበት ቴክኖሎጂው አማካኝነት የቅርብ ያህል ከብዙዎች ጋር ቤተሰብ በመሆን በርካታ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን የምታከናውን ትጉ ሴት ናት። የምትሠራቸው የበጎ አድራጎት ሥራዎች ተሳክተው ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን አግኝተው ፤ መታከም የሚገባቸው ሰዎች መታከሚያ ገንዘብ አግኝተው ሲታከሙ እንደገና ለምስጋና ወደርሷ ይመጣሉ። ከነዚህ ውስጥ እጅግ በጣም የማትረሳት ህፃን ነበረች ።

ህጻናንም እንዲህ ታስታውሳለች ‹‹የዛሬ ሶስት ዓመት አንድ አባት ደወለለኝና የስድስት ወር ህፃን ልጁ የልብ ህመም ገጥሟት ለህክምና ወደ ህንድ መሄድ ነበረባት ነገር ግን ለመታከሚያ የሚሆናት ገንዘብ ከሰዎች ተሰብስቦ እንደጎደለ ነገረኝ። እኔም የህፃኗን መታመም እርግጠኛ ከሆንኩ በኋላ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ሳይወጣ የማውቃቸውን ጓደኞቼን ፣ ወዳጆቼን ጠየኳቸው ገንዘቡንም በቶሎ ማግኘት ችዬ ወደ ህንድ ሄዳ ህክምናዋን አድርጋ መመለስ ቻለች ። እኔም ፈጣሪዬን አመስግኜ ወደ ሌሎች ጉዳዮቼ እና እገዛ ወደሚያስፈልጋቸው ሰዎች ፊቴን አዞርኩኝ ፤ ከዚያም ከዓመታት በኋላ አባቷ ይህቺ በልብ ህመም ተይዛ የነበረችው ህፃን ልጅ ተሽሏት አድጋ እየቦረቀች ልደቷን ስታከብር የሚያሳይ ምስል ከመልዕክት ጋር ላከልኝ። ይሄ ለኔ በጣም ትልቅና የማረሳው ታሪክ ነው።››

ሕይወት ለተቸገሩ ሰዎች ለመድረስ የልደት ቀንዋንም ለዚህ መልካም ነገር ማዋል ከጀመረች ሰንበትበት ብላለች። መነሻው የነበረው ግን እንዳጫወተችን የመጀመሪያ ልጇን የአንደኛ ዓመት ልደት ከተለመደው የልደት አከባበር ወጣ በማለት በባለቤቷ ሃሳብ አመንጪነት በኢትዮጵያ አዲስ አበባ የሚገኝ ከበበ ፀሃይ የወደቁ ህፃናትን አንስቶ የሚያሳድግ ማዕከል ከሚኖሩ ህፃናት ጋር ለማክበር ወሰኑ ለማዕከሉም ከእንግዶቻቸው የሚሰጣቸው ስጦታ የልጆች የተረት መፅሃፍ እንዲሆኑ በማድረግ ሃሳቡን በማህበራዊ ገፅ ላይ በማጋራት ከተለያዩ ግለሰቦች እና የመፅሃፍ መደብር ያላቸው ሰዎች ሃሳባቸውን ደግፈውት ብዙ መፅሃፎችን መሰብሰብ ቻሉ።

የሰበሰቡትን መፅሃፍ ወደ ማዕከሉ ይዘው በመሄድ የልጃቸውን ልደት አክብረው የመፅሃፍ ስጦታውንም ለማዕከሉ አበረከቱ።

ሕይወት ከአራት ዓመት በፊት ከልብ ህሙማን ህፃናት ጋር ተቀራርባ በምትሰራበት ፤ ዓላማውን ለብዙዎች እያስረዳች ድጋፍ በምታሰባስብበት ሰዓት የልደቷ ጊዜ ደረሰ እናም የልደት ቀኗ ከመድረሱ በፊት ሰዎች የሚሰጧትን የመልካም ልደት ስጦታ በገንዘብ ተቀይሮ የልብ ህሙማን ህፃናት ህክምና ይውል ዘንድ በማህበራዊ ገጽ ላይ አጋራችው። ሃሳቡን ባጋራችበት የመጀመሪያ ልደቷ ላይም በጎ ሃሳቧን በተጋሩ መልካም ሰዎች አማካኝነት አንድ ሚሊዮን ብር ማግኘት ቻለች ይህም ለ10 ህፃናት ህክምና ዋለ።

ይህ ለርሷ ጥሩ ምልክት እና ብርታት ነበር ። ሁለተኛው ዓመት ላይ ደግሞ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር ሰብስባ 12 ህፃናት ሲታከሙ ከዛ በተጨማሪም ተስፋ ለህፃናት የካንሰር ህሙሙማን ማዕከል ውስጥ በአካል ባትገኝም በቦታው ለሚገኙ ህፃናትና እና የህፃናቱ ቤተሰቦች የምሳ ግብዣና ለህፃናቱ የሚስፈልጋቸውን ስጦታዎች በማበርከት ደስታቸውን በመፍጠር ተከብሮ አለፈ ።

ሕይወትና የኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ማዕከል ቤተሰባዊነታቸው እየጠነከረ ሄዷል። በማዕከሉ ህክምና ለማግኘት ወረፋ የሚጠብቁ ህፃናት ቁጥር ከሰባት ሺህ በላይ ሲሆን፣ማዕከሉ ያለው አቅም እና የሚያስተናግዳቸው ታካሚዎች ቁጥር የሚመጣጠን አልነበረም ። እናም ልባሟ ሕይወት በዚህ የልደት ቀኗ ላይም ከገንዘብ ባሻገር በልብ ህመም ተይዘው ለህክምና ወረፋ የሚጠብቁ ህፃናትን ለማገዝ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ማዕከል ያለበትን የህክምና መርጃ መሣሪያ እጥረት በመረዳት ሌላ የተሻለ ሃሳብ አመጣች ፤ በዚህም ከአንድ ብርቱ ሁለት መድሃኒቱ ሚባለው እንዲሁ አይደለምና ከሌሎች ልበ-ቀናዎች ጋር በመተባበር ኪዩር ከተባለ ዓለምአቀፍ ድርጅት 50 ሚሊዮን ብር የሚገመት የህክምና ቁሳቁስ ድጋፍ አገኘች።

ሕይወት ባለትዳር እና የሶስት ልጆች እናት ነች። ሕይወት ባለቤቷን የተዋወቀችው ገና የ 11ኛ ክፍል ተማሪ በነበረችበት ወቅት ነበር ። ‹‹ከተዋወቅን ጊዜ ጀምሮ አብረን እንኖር ነበር ብዙ ውጣ ውረዶችን ከፍታ እና ዝቅታዎችን አሳልፈናል ትናንት ያሳለፍነው ሕይወት ዛሬያችንን ሰርቶታል አሁን ባለንበት ደግሞ ፈጣሪ በልጅ ባርኮናል ይህም የሆነው ከፈጣሪ ነው አጋርነት ፤ በትዳር መጣመር ማለት አንዱ ያንዱን ሸክም መሸከም ኀዘንንም ሆነ ደስታን በጋራ ማሳለፍ ነው›› ስትልም ስለትዳሯ አጫውታናለች።

ሕይወት ወደፊት ብዙ ህልሞች እና ልታደርጋቸው የምትፈልጋቸው ሃሳቦች አሏት ፤ ከኢትዮጵያ የልብ-ህሙማን ማዕከል ጋር በተገናኘ የምታደርገውን የበጎ ሥራ ድጋፍ አጠናክራ የምትቀጥለው እንጂ የምትተወው እንዳልሁነም ትገልፃለች ትፈልጋለች። ከዚህም ባሻገር ከህፃናት ትምህርት ቤቶች ጋር ፣ አረጋውያንን ከማገዝ ጋር በተያያዘ ወደፊት ሰፊ ሥራዎችን የመስራት ሃሳብም ጭምር አላት ።

ሕይወት በምትሠራቸው በጎ ሥራዎች ከተለያዩ አካላት ሽልማቶች ተበርክቶላታል። ከተበረከቱላት ሽልማቶች ውስጥ በሞንቶጎሞሪ ከተማ ‹‹ቤስት ሰርቪስ አዋርድ›› ማለትም የምርጥ አገልግሎት ሽልማት ዘርፍ አለ። በዚህ ዘርፍ እጅግ በጣም ትልልቅ የበጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ የተሳተፉ ሰዎች የሚታጩበት እና የሚሸለሙበት መድረክ ነው። በዚህ መድረክ ላይም ሕይወት እጩ ሆና ቀርባለች ይህም ለሷ ትልቅ ትርጉም እንዳለው ትናገራለች ።

ሌላኛው ሽልማት መቀመጫውን በኢትዮጵያ ያደረገው የጣፋጭ ሕይወት ሽልማት ማህበራዊ ድህረ-ገፅን ለበጎ ዓላማ መጠቀም በሚል የኢንስታግራም ማህበራዊ ገፅን በመጠቀም ላበረከተችው አስተዋፅኦ የዋንጫ ሽልማት ተበርክቶላታል። ሌላኛው ሽልማት ከሠራቻቸው የበጎ ሥራዎች ከተበረከቱላት ምስጋናዎች ፣ ሽልማቶች እና እውቅናዎች ውስጥ ግን እሷ አብልጣ የምትወደው እና የምታስታውሰው በኢትዮጵያ የልብ ህመም ማዕከል የተሰጣት ሰርተፍኬት እና በማዕከሉ ውስጥ በሷና በሌሎች እገዛ ታክሞ የዳነ አንድ ህፃን ልጅ ለልደቷ የሰጣትን ስጦታ አትረሳውም ‹‹ከህፃናቱም ሆነ ከማዕከሉ የሚሰጡኝን ስጦታዎች ቤቴ አስቀምጬ ልጆቼ አድገው ሲጠይቁኝ የምናገረው ታሪክ ለሌሎች በጎ ስለመሆን የማስተምርበት ታክመው የዳኑ ህጻናት መሆናቸውን ስነግራቸው ልጆቼ ልባቸው ተነክቶ ስለመስጠት የሚማሩበት ስለሚሆን በጣም ደስተኛ ነኝ›› ስትል ትገልፃለች ።

ከሽልማቶቹ ባሻገርም በተለያየ ጊዜ ላደረገቻቸው መልካም ሥራዎች ከመቄዶኒያ የአረጋውያን ማዕከል ፣ ተስፋ አዲስ የካንሰር ህሙማን ህፃናት ማዕከል ፣ ሰሊሆም የአዕምሮ ህሙማን ማዕከል ፣ ከኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ማዕከል የምስጋና የምስር ወረቀት ተበርክቶላታል። ነገር ግን አሁንም ቢሆን ሕይወት ሳትል የማታልፈው አንድ ነገር አለ ‹‹እነዚህ ሁሉ ሽልማቶች የኔ ብቻ አይደሉም የባለቤቴና የልጆቼ ናቸው። ምክንያቱም እነዚህን ሥራዎች ስሠራ ከነሱ ሰዓት እየቀነስኩ ነው የማደርገው ፣ በሀገር ውስጥም በውጭም የሚገኙ በገንዘብ ፣ በሃሳብ ደግፈውኛል ወዳጆቼ ጓደኞቼ ከጎኔ ነበሩ›› በማለት ታመሰግናለች።

ሕይወት እስከዛሬ ድረስ በግልም ከሌሎች ጋር በመሆንም በምትሠራቸው የበጎ አድራጎት ሥራዎች ባሰበችው ልክ ታስኬድ ዘንድ የረዷትን ባለቤቷን ፣ ልጆቿን ፣ ቤተሰቦቿን ፣ ወዳጆቿን ፣ የኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ማዕከል ዋና ዳይሬክተርና በአሜሪካ የሚገኝ ተወካይ ሌሎች ተባባሪ ድርጅቶች ታመሰግናለች። የተለያዩ ርዳታ የሚፈልጉ የብዙ ሰዎችን ርብርብ የሚጠይቁ የበጎ ሥራዎችን በማህበራዊ ገፅ ላይ ለማጋራት ይዛ በምትወጣበት ጊዜ በተለያየ የዓለም ክፍል ሆነው ነገር ግን በፍላጎትና በአመኔታ ያገዟትን ሁሉንም ኢትዮጵያውያን ጭምር ታመሰግናለች ።



# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

አዲስ ዘመን ድሮ ዛሬም ተመዘው የማያልቁ ብዙ የትናንት ትውስታዎች አሉት። ከእነዚህም መካከል ለዛሬ ቆየት ያሉና በይዘታቸው ወጣ ያሉ አስገራሚ ክስተቶችን ከጋዜጣው የዘገባ ማህደሮች መዘን እናስታውሳለን። በአለቃው አይን ሚጥሚጣ ጨምሮ በጩቤ የወጋው ግለሰብ ለፍርድ ስለመቅረቡ፣ የተሰረቀ የበግ ስጋ የበሉት ግለሰቦች የተከተላቸውን መዘዝ፣ "የስም ነገር ሲነሳ" ከአድማስ ገጽ ልዩ እትም እንዲሁም ደግሞ ከዚህም ከዚያም የተወሰደች አንዲት ሃሳብ በማሳረጊያው ተካተዋል።

**በአለቃው አይን ሚጥሚጣ ጨምሮ 5 ዓመት ተቀጣ**

ደመወዝ አላስጨመርክልኝም፤ በየጊዜው ትጨቀጭቀኛለህ በማለት ቂም ወርሶ በአለቃው ሁለት አይን ውስጥ ሚጥሚጣ ጨምሮ በጩቤ የወጋው አባተ አካሉ በአምስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ትናንት ተፈረደበት።

ተከሳሹ ታህሳስ 10 ቀን 1963 ዓ.ም ከጠዋቱ 1 ሰዓት ላይ ከአለቃው አስቀድሞ ገብቶ እጅ እንደ መንሳት ሞክሮ፣ ሚጥሚጣ በወረቀት ጨቤና ቆንጨራ ይዞ ሚጥሚጣውን በአለቃው አይን ጨመረ። አለቃው ዓይናቸውን በሁለት እጃቸው ሲሸፍኑ፤ በጩቤ ከጀርባቸው ላይ ወግቶ ማቁሰሉን የቀረበበት የአቃቤ ሕግ ክስ ያስረዳል።

አባተ ወንጀሉን የፈጸመው በመናገሻ አውራጃ አቃቂ በሰቃ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኢንዶ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ መስሪያ ቤት ውስጥ ነው። አለቃውን አቶ ተስፋዬ በቀለን ለመግደል ሲሞክር የገላገሉትን አቶ ንጉሴ ለማን በጩቤ ከግራ ጭናቸው ላይ ማቁሰሉንና በሕዝብ መተባበር የተያዘ መሆኑን የአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት የቀረበበት የዓቃቤ ሕግ ክስ ይዘረዝራል።

ወንጀለኛው መጀመሪያ ፍርድ ቤት ሲቀርብ፤ጥፋተኛ አይደለሁም ወንጀሉንም አልፈጸምኩም በማለት ክዶ፤ ችሎቱ አቃቤ ሕግ በማስረጃ ስለተረጋገጠበትና በመከላከያ ስላልተደገፈ፤ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦበት ቅጣቱ ተወስኖበት ወይኒ ቤት ገብቷል።

**(አዲስ ዘመን መስከረም 4 1964 ዓ.ም)**

**መኪናዋ ስትጋጭ ነጂው በመስኮት ሾልኮ ሕይወቱ ዳነ**

ኅዳር 16 ለ17 አጥብያ ከለሊቱ 6 ሰዓት ላይ በደብረዘይት መንገድ ከመሿለኪያ በታች ጀንዊሊያም ዳርሊን የተጋጨበት አውቶሞቢል መላ አካሏ ተንከታክቶ፤ ግንባሯ ወደ ኋላ ተመልሶ ሞተሯ ተበታትኖ ከአውራ መንገድ ላይ ተዝረክርኳል።

መኪናዋ ከቀኝ ወደ ግራ በመተጣጠፍ ከመሃል ጎዳናው የሚገኘውን የፍሎረሰንት መብራት መያዣ ምሰሶ ገጭታ ስታንብጠው መላ አካሏ ተሰባብሮ የአንድ እግሯ ጎማ ከቀኝ ወደ ግራ 30 ሜትር ተሽከርክሮ ከጉድጉአድ ውስጥ ገብቷል።

በአሰቃቂ ሁኔታ በደረሰው አደጋ 29 ዓመት የሚሆነው እንግሊዛዊ መምህር ከፊት በደረሰው ቁጥር 21094 በሆነች አነስተኛ ሬኖ መኪና ከመብራት ምሰሶ ጋር በአደገኛ ሁኔታ ተጋጭታ ብትንትኗ ወጥቶ ከአገልግሎት ውጪ ስትሆን፤ በግጭት ምክንያት ወደኋላ ተስፈንጥሮ መስኮቱ ተከፍቶ ሲወድቅ ምንም የመቁሰል አደጋ ሳይደርስበት መዳኑ ታውቋል።

**(አዲስ ዘመን ሕዳር 18 ቀን 1964ዓ.ም)**

**የተሰረቀ የበግ ስጋ የበሉት ሰዎች 500 ብር ተቀጡ**

ደብረብርሃን (ኢ-ዜ-አ) ተሰርቆ የታረደ በግ ስጋውን ተመግበዋል ተብሎ ክስ በቀረበባቸው የወረዳው ምክትል ገዢና የወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ምክትል አዛዥ፤ እያንዳንዳቸው 500 ብር መቀጫ እንዲከፍሉ የተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ፍርድ ቤት ባለፈው ሳምንት ፈረደ።

በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው የገንዘብና የእስራት ቅጣት የተበየነባቸው በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ጋዛት በሞረት ወረዳ የጅሑር ምክትል ወረዳ ገዥ የሆኑት አቶ ስሜ አልታዬና የዚሁ ምክትል ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ የሆኑት 50 አለቃ ነጋሽ ሀብተ ሚካኤል ናቸው።

በሁለቱም ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ እንደሚከተለው ግንቦት 8 ቀን 1962 ዓ.ም የአቶ ሸዋረጋ ተክሌ ንብረት የሆነ አንድ በግ ሙክት ተሰርቆ ሰው በማይኖርበት ወና ቤት ውስጥ እንደታረደ፤ በነጭ ለባሽ ወታደሮች መከታተል ተገኘ። ከዚያም የታረደው ሙክት ወደ ወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ተወስዶ በኢግዚቢትነት እንደተቀመጠ ሁለቱ ሰዎች ቆዳውን አስገፍፈው ስጋውን በመመገባቸው የወንጀሉን ምርመራ አደናቅፈዋል።

በቀረበው ክስ ምርመራው ተጣርቶ የሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ እንደየጥፋታቸው እያንዳንዳቸው 500 ብር መቀጫ እንዲከፍሉ ተበይኖባቸዋል። ነገር ግን ገንዘቡን ባይከፍሉ እያንዳንዳቸው በስድስት ወር እስራት እንዲቀጡ የተፈረደባቸው ሲሆን ገንዘቡን ባለመክፈላቸው ወደ ወይኒ ቤት መላካቸውን የአውራጃው ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ታደሰ አልቴ ገለጡ።

**የስም ነገር ከተነሳ**

በአንድ ወቅት በእሁድ የራዲዮ ፕሮግራም ሁለት ኢትዮጵያውያን ልጃቸውን አፍ ያስፈቱት በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሆኑንና ስሙም ጆንሰን መባሉን ስንሰማ አንዳንዶቻችን አስገርሞናል። የራስን ንቆ የሰውን ማክበር መሰለንና።

በአንዳንድ አካባቢ የልጆች ስም ከአባት ስም ጋር እንዲገጥም ወይንም ደግሞ የአባትና የልጅ ተመሳሳይነት እንዲኖረው ሆኖ ይወጣል። ይህንን አይነቱን ለማየት ለወደፊቱ እንቃጠርና ለዛሬው የመንዞችን ስም አወጣጥ ለአይነት ያህል ላቅርብ።

ለወንድ- ሺናባቸው፣ አብጠው፣ አጋጨው፣ ደምለው፣ ጠምሰው፣ ውቃው፣ አምለው፣ ግፋው፣ ጨቡዴ፣ ጠፍሬ፣ አባርቄ፣ አጉኔ፣ አይተንፍሱ፣ ጭጭይበሉ፣ ይፍሩ፣ይሸበሩ፣ ይጨነቁ፣ ላንተይደሩ።

ለሴት- ይብረኩ፣ ይስገዱ፣ ውርጭአለቁ፣ አብረው ያምሹ፣ ይሰለፉ፣ ይሻሙ፣ ማን ከልክሎሽ፣ አንቺ አያህሎሽ፣ ሁሉግርጌሽ፣ እርገጭ ይጠለሉብሽ፣ ይዝበጡ።

**(አዲስ ዘመን ጥቅምት 4 ቀን 1977ዓ.ም)**

**ከዚህም ከዚያም**

**"ጠረን ተባዕት ለእንስት ጤንነት"**

"ሴቶች የወንዶችን የአካል ጠረን ይላመዳሉ። መላመድ ብቻ ሳይሆን ከተባዕቱ አካል በተለይም ከብብት አከባቢ በላቦት ታጅቦ የሚወጣው ጠረን በሚተኙበት በሚተቃቀፉበትና በፍቅር ጭውውት ወቅት ሁሉ እየመነጨ ስለሚያውዳቸው ለዛውን ጠንቅቀው ያውቁታል። ማወቅ ብቻ ሳይሆን የተባውን ስሜታቸውን በማነቃቃት ወደ ፍትወት ይወስዳቸዋል።

የወንዶች የአካል ጠረን ጉልበት በዚህ ብቻ አይወሰንም። ሌላም ዓቢይ ጥቅም አለው... በማለት ወ/ሮ ዊኒፊሬድ ኮትለር የጠረንን ሚስጥራዊ ኃይል በዝርዝር የሚያትት ድርሳናቸውን ለአደባባይ አውለውት ተቀባይነት እያገኘ ነው።

**(አዲስ ዘመን ሰኔ 7 ቀን 1979 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## ለኮቪድ ክትባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ሳይንቲስቶች የኖቤል ሽልማትን አሸነፉ

የኖቤል የጤና እና የፊዚዮሎጂ ሽልማት ኤምአርኤንኤ የተባለውን የኮቪድ ክትባትን ለመሥራት የሚያስችል ቴክኖሎጂን ላዳበሩ ሁለት ሳይንቲስቶች በጋራ ተሰጠ። ፕሮፌሰር ካታሊን ካሪኮ እና ፕሮፌሰር ድሪው ዋይስማን የዚህን ዓመት የኖቤል የጤና ሽልማትን በጋራ ማግኘታቸው ይፋ ሆኗል።

ቴክኖሎጂው የኮቪድ ወረርሽኝ ከመከሰቱ በፊት በሙከራ ደረጃ ላይ የነበረ ሲሆን፣ አሁን በዓለም ዙሪያ በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ሰዎች ወረርሽኙን ለመከላከል ተሰጥቷል። ይህ ቴክኖሎጂ በአሁኑ ጊዜ ካንሰርን ጨምሮ ለሌሎች በሽታዎች ጥቅም ላይ ለማዋል ምርምር እየተደረገበት ነው።


የኖቤል ሽልማት ኮሚቴው ሁለቱን ሳይንቲስቶች ይፋ ሲያደርግ "በሰው ልጅ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ ላጋጠመው ከፍተኛ የጤና ስጋት ሁለቱ ተሸላሚዎች ቀደም ሲል ባልታየ ሁኔታ ክትባት በማዳበር በኩል አስተዋጽኦ አበርክተዋል" ብሏል።

ሳይንቲስቶቹ የኖቤል ሽልማትን ማሸነፋቸው ዛሬ ሰኞ ጠዋት የተነገራቸው ሲሆን፣ የዓለማችን ዋነኛ ሽልማት አሸናፊ ሆነው በመመረጣቸው "ደስተኛ" መሆናቸውን መናገራቸው ተዘግቧል። ክትባቶች የሰዎች ተፈጥሯዊ በሽታን የመከላከል ሥርዓት ቫይረስ እና ባክቴሪያን የጤና ጠንቆችን እንዲለይ እና እንዲዋጋ ያደርጋሉ።

የተለመደው ዓይነት በሽታን መከላከያ ክትባቶች የሚዘጋጁት ከሞቱ ወይንም ከተዳከሙ ቫይረሶች ወይም ባክቴሪያዎች ነው። ከዚህ አንጻር ተሸላሚዎቹ ሳይንቲስቶች የፈጠሩት ኤምአርኤንኤ የተባለው ቴክኖሎጂ ግን ክትባት እንዲሠራ ፈጽሞ የተለየ መንገድን ይከተላል ተብሏል።

የኮቪድ ወረርሽኝ በተከሰተበት ጊዜ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተደረጉት ሞደርና እና ፋይዘር/ባዮንቴክ ክትባቶች ይህንን ኤምአርኤንኤ ቴክኖሎጂን መሠረት አድርገው ነው የተሰሩት። ሁለቱ ዶክተሮች ካሪኮስ እና ዋይስማን አብረው መሥራት የጀመሩት በአውሮፓውያኑ 1990ዎቹ በአሜሪካው ፔንሲልቬኒያ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሲሆን፣ በኤምአርኤንኤ ቴክኖሎጂ ላይ የነበራቸው ፍላጎት ብዙም የሚያዛልቅ አይደለም ተብሎ ታስቦ ነበር።

ይህ ቴክኖሎጂ በሰው ልጅ አካል ውስጥ እንደ አስተርጓሚ ሆኖ የሚሠራ ነው። ቴክኖሎጂው የሰው ልጅ ዘረመል (ዲኤንኤ) ላይ ያሉ መረጃዎችን ተንትኖ ለመረዳት የሚያስችል ነው። የሚገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግም የሰው ልጅን የሚያጋጥሙ የጤና ጠንቆችን በዝርዝር በመረዳት፣ ተፈጥሯዊው በሽታን የመከላከያ ሥርዓት ቫይረስ ወይም ባክቴሪያዎችን ለመዋጋት እና ለማጥፋት የሚያስችለውን ዕውቀት እንዲያዳብር ያደርጋል።




ለኮቪድ ክትባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ሳይንቲስቶች የኖቤል ሽልማትን አሸነፉ

ይህ ኤምአርኤንኤ ቴክኖሎጂን በተለይ በኮቪድ ወረርሽኝ ወቅት በታማሚዎች ውስጥ በሽታውን ለመቋቋም እና ለማጥፋት የሚያስችል ሁኔታን በመፍጠር ወሳኝ አስተዋጽኦ አድርጓል።ዶ/ር ካታሊን ካሪኮ በአሁኑ ጊዜ በሃንጋሪ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ፕሮፌሰር ሲሆኑ፣ ዶ/ር ድሪው ዋይስማን ደግሞ እዚያው ፔንሲልቬኒያ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ፕሮፌሰር ሆነው እያገለገሉ እንደሚገኙ ቢቢሲ ዘግቧል።

## የኦባማ ሠዓሊ የፕሬዚዳንት ሳህለወርቅን ጨምሮ የሌሎች የአፍሪካ መሪዎችን ሥዕሎች ለዕይታ አቀረበ

የአሜሪካን የቀድሞ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ምስል (ፖርትሬት)ን በመሳል ዝናን ያተረፈው ኬሂንዴ ዋይሊ የኢትዮጵያን ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴን ጨምሮ ሌሎች የአፍሪካ መሪዎችን የሚያሳዩ የጥበብ ሥራዎቹን በፈረንሳይ ለዕይታ አቀረበ።

ኬሂንዴ በባራክ ኦባማ ሥራው የአሜሪካን መሪ ፕሬዚዳንታዊ ምስል (ፖርትሬት) በመሳል የመጀመሪያው አፍሪካዊ አሜሪካዊ በመሆንም ታሪክ ሰርቷል። በአሁኑ ወቅት 11 የአፍሪካ መሪዎችን የሚያሳዩ የሥዕል ሥራዎቹን ለዕይታ አቅርቧል። ከኢትዮጵያዋ ፕሬዚዳንት በተጨማሪ የጋናው ፕሬዚዳንት ናና አኩፎ አዶ፣ የናይጀሪያው የቀድሞ ፕሬዚዳንት አሉሴጉን አባሳንጆ በመሪዎቹ ምስሎች (ፖርትሬት) ሥዕሎች ከተካተቱበት ይገኙበታል።

'ኤ ሜዝ አፍ ፓወር' የሚል ርዕስ የተሰጠው የሥዕል አውደ ርዕዩም በፈረንሳይዋ መዲና ፓሪስ በሚገኘው 'ሙዜ ዱ ኬ ብራንሊ- ጃክ ዢራክ' ሙዚየም ለዕይታ ቀርቧል። አውደ ርዕዩም እስከ መጪው የአውሮፓውያኑ ዓመት ጥር 2024 ድረስ ክፍት ሆኖ ይቆያል ተብሏል።

ኬሂንዴ የመሪዎቹን ምስሎች (ፖርትሬት) ሥዕሎችን ለመሳል 10 ዓመታትን እንደፈጀበት ስለ ጥበብ ሥራዎቹ በተዘጋጀ ዘጋቢ ፊልምም ላይ ተናግሯል። ከአውሮፓውያኑ 2012 ጀምሮ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በመዘዋወር ከተለያዩ መሪዎች ጋር ተገናኝቷል። እንዲሁም ከ17ኛው እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ስለነበሩ የነገሥታት፣ የመኳንንት እና ወታደራዊ ሥዕሎችን አጥንቷል እንዲሁም ውይይት አድርጓል።

በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ያደረጋቸው ውይይቶች እና ጥናቶች ላይ መሠረት በማድረግም ነው የመሪዎቹን ምስል (ፓርትሬት) የሳለው። እነዚህ ሥዕሎች በዘመኑ የአፍሪካ መሪ መሆን ምን ማለት እንደሆነም ያሳያሉ። "ሥዕሎቹ የመሪነትን ሥፍራን ነው የሚያሳዩት። ተመልካቾች የዕይታ አድማሳቸውን አስፍተው በአፍሪካ ውስጥ ያለውን ጥበብ፣ አፍሪካን ማዕከል በማድረግም ሥልጣንን እንዲመለከቱ የቀረበ ግብዣ ነው" ማለቱን የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።



## ከሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ውጤታማዎችን በማመስገን ስኬታማዎችን መፍጠር

**ታምራት ተስፋዬ**

ደራሲ ጆን ሄንሪ ጆዌት ምስጋናን ሲገልፀው፣ «ምስጋና ክትባትና ፀረ መርዝ እንዲሁም የቆሰለውን የሚጠግን መድሃኒት ነው» ይላል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ምስጋና የሚለውን ቃል በተለያዩ መዝገበ ቃላት ሰፊ ትርጉም ይሰጠዋል። በተለይ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ጥናት ተቋም ባሳተመው መዝገበ ቃላት አመሰገነ ማለት «ለሥራው መልካም ሥራ ተገቢው ቦታ ተሰጠው» ይላል።

ምስጋና በየትኛውም ሃይማኖት መነፅር ከተመለከትነው ቅዱስ ተግባር ነው። በምድራዊው ዓለም ቢሆን ከግለሰብ አንስቶ በተቋም ደረጃም ሊተገበር፣ ሊለመድና ሊዳብር የሚገባው መልካም ተግባር ነው። የምሥጋና ደንቡም ክብር ለሚገባው ክብር መስጠት ነው። ይሁንና እንዳለመታደል ሆኖ በአገራችን ብዙዎቻችን በምስጋና ውስጥ ያለው ኃይል ጠንቅቆ አይገባንም። ከሁሉ በላይ በተለይ በተቋም ደረጃ ውጤታማዎችን ማመስገንም ሌሎች ብዙ ውጤታማዎችን እንደሚፈጥር በበቂ መልኩ አልተረዳንም። መልካምና ውጤታማ ፈፃሚዎችን ማመስገን፣ እያከናወኑት ላሉት አወንታዊ እርምጃና ላስመዘገቡት ውጤት እውቅና መስጠትም እርካታው ከተመስጋኙ በላይ ለአመስጋኙም እንደሚተርፍ አልገባንም።

እውቅና ስንሰጥና ስናመሰግን የመጀመሪያው፣ የምናመሰግነው አካል ምስጋናው ይገባዋልና ደስተኛ ይሆናል። በከፍተኛ ሞራል ይበልጡን ለሥራ ይነሳሳል። ማመስገን ለአመስጋኙ ደስታ፤ ለተመስጋኙ ለቀጣይ የሕይወት ምዕራፉ ዓይነተኛ ጥቅም ነው።

በሁሉ ረገድ ታታሪና ለውጤታማነት አቅም ለመፍጠር ሌት ተቀን የሚጥሩ አይቶ እንዳላየ ሰምቶም እንዳልሰማ መቁጠር በአንፃሩ አደጋው በብዙ መልኩ የሚታኝ ነው። ከሁሉ በላይ ታታሪዎች ልፋታቸውን ከቁብ የሚቆጥረው እንደሌለ እንዲሰማቸውና ተነሳሽነት እንዲጠፋባቸው፣ የእሳት ወላፈን እንደጎበኘው ላስቲክ



እንዲኮማተሩ፣ ያደርጋል። ምስጋና እና እውቅና መስጠት ልምድ ማድረግ ከተቻለ ግን እንዲህ ዓይነቶቹ የቅሬታ ስሜቶች ሊቀረፉ እንደሚችሉ ጥርጥር የለውም።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በአገራችን ውጤታሞችን በማመስገን ውጤታሞችን መፍጠር እንደሚቻል የገባቸው የግልም ሆነ የመንግስት ተቋማትን እየተመለከትን እንገኛለን። ከእነዚህ ተቋማት መካካልም ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ከግንባር ቀደምቶቹ ተርታ ሊጠቀስ ይችላል። ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ በ2015 ዓ.ም የተሰጡትን ሀገራዊ ተግባርና ኃላፊነት በመወጣት ሂደት እንዲሁም ሀገራዊ ራዕይና ግብን ለማሳካት የሚያግዙ የተለያዩ ውጤታማ ተግባራትን አከናውኗል። የ2015 ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ግምገማና የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ ውይይት ሲያካሂድም ይህን ስኬቱን ‹‹አወቁልኝ›› ብሏል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የዩኒቨርሲቲው እቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክተር አቶ ጥበቡ ታደሰ እንደሚሉት፤ ዩኒቨርሲቲው በመማርና ማስተማር፣ ጥናትና ምርምር፣ በማሕበረሰብ አገልግሎት እንዲሁም አጠቃላይ በአካዳሚክና በአስተዳደር ሥራዎች ላይ አበረታች ውጤት አስመዝግቧል። ሀገራዊ የዋጋ ግሽበቱን ተከትሎ ያጋጠመው የበጀት እጥረት እንደዋና ተግዳሮት ቢሆንም የዩኒቨርሲቲው አፈፃፀም ግን 84 በመቶ ስኬታማ ነበር።

ዩኒቨርሲቲው በዓመቱ ወደ ትምህርት ጥራት የሚደረገውን ጉዞ ምቹ ከሚያደርጉ መደልድሎች በዋነኛነት የሚጠቀሰውን የመውጫ ፈተና (Exit exam) እንዲሁም የ12ተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና አሰጣጥ ላይ በሰራው ሥራም ስኬታማ ነበር። ዩኒቨርሲቲው በ2015 በጀት ዓመትም የተሰጡትን ሀገራዊ ተግባርና ኃላፊነት በመወጣት ሂደት በተለይ በማሕበረሰብ አቀፍ አገልግሎት የአካባቢውን ማህበረሰብ ሕይወት ለማሻሻል በሚያግዙ የተለያዩ ተግባራት ዙሪያ ሥራዎችን አከናውኗል። ከመማር ማስተማርና ምርምር ሥራው ባሻገር በተለያዩ ሰዋዊ የበጎ አድራጎትና መልካም ተግባራት ላይም ተሳታፊ ነበር። እንዲሁም ማሕበረሰብ ተኮር ድጋፎች ላይ በተለይም ‹‹ለወገን ደራሽ ወገን ነው›› በሚል የመልካምነት፣ የአጋርነት መንገድን በመያዝ በተለይ በቦረና ድርቅ ለተጎዱ ወገኖች ድጋፍ አድርጓል። ለአብነት እነዚህ ተዘረዘሩ እንጂ ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ስኬታማ ሥራዎች አከናውኗል፡፡

ውጤታሞችን በማመስገን ውጤታሞችን መፍጠር እንደሚቻል የሚያምነው ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ‹‹ለውጤታማ አፈፃፀማችን ሁላችሁም አሻራችሁ አለበት፣ ለዚህም ምስጋና እና እውቅና ይገባችኋል›› ሲል ለመላ ሰራተኞች የምስጋና ፕሮግራም ከቀናት በፊት አዘጋጅቶ ነበርም። በዚህ የእውቅና ምስጋና ፕሮግራም ላይም የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮችን ጨምሮ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ ሰራተኞች ተካፋይ ሆነዋል።

በመርሃ ግብሩ ላይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶክተር ገናነው ጎፌ ባስተላለፉት መልክዕት፤ ዩኒቨርሲቲው በዓመቱ ያስመዘገበው ሁለንተናዊ ስኬት የሁሉም ሰራተኞች ተሳትፎ ውጤት መሆኑን ጠቁመው፤ ምስጋና ይገባቸዋል። ይህ እውቅናም የዚሁ አካል መሆኑን በመግለጽ ‹‹እንኳን ደስ አላችሁ›› ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው በተለይም የመውጫ ፈተናን (Exit Exam) ፈተናን በብቃት በማስፈፀም እና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተማሪን በማሳለፍ ትልቅ ስኬትን አግኝቷል። በአገሪቱ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችም በማሳለፍ ምጣኔ አራተኛ ደረጃን ይዟል። ከአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎች (comprehensive) መካከል ደግሞ የአንደኛ ደረጃን ለመያዝ በቅቷል። ይህ ስኬቱም በ2025 ዓም አሳካዋለሁ ያለውን ራዕይ በማሳካት ረገድ ከወዲሁ ግቡን መምታት መቻሉን አመላካች ተደርጎ የሚወሰድ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በእለቱ ለተመዘገቡ ስኬቶች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በላቀ መልኩ ላበረከቱ ምሥጋና እና የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል። የምሥጋና ዕውቅና ያገኙት ሠራተኞችም ዩኒቨርሲቲው ያበረከተላቸውን ምሥጋና በማድነቅና ይበልጥም ተነሳሽነትን እንደሚፈጥር በመጠቆም፣ በቀጣይ ለዩኒቨርሲቲው ሁለተናዊ ስኬት እንደሚተጉም ‹‹አትጠራጠሩ›› ብለዋል።

## ከኢፌዴሪ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ተጨማሪ ጥረትን የሚጠይቀው የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት

**ሰላማዊት ውቤ**

በዓለማችን በተለይም በሀገራችን በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ከሚሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል አካል ጉዳተኞች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። ይሁንና የቁጥራቸውን ያህል ተጠቃሚ እየሆኑ ነው ማለት አያስደፍርም። እንደ ሀገር ያለውን ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጡ ረገድ የአንበሳውን ድርሻ ወስዶ እየሰራ የሚገኘው ሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለተጠቃሚነታቸው ተጨማሪ ሥራዎች መሰራት እንዳለበት ያሳስባል።

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የአካል ጉዳተኞች የአድቮኬሲና መብት ጥበቃ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሲሳይ ጥላሁን እንደሚሉት፤ አካል ጉዳተኞች በጉዳታቸው ምክንያት የተለየ ትኩረት ይሻሉ። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ይህን ታሳቢ በማድረግ እንደ አዲስ ከተዋቀረ ጀምሮ በየመስኩ ላለው ተጠቃሚነታቸው ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ ቆይቷል። ለአብነት በ2015 በጀት ዓመት ከ3 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር በላይ ሀብት በማሰባሰብ 33 ሺህ 419 አካል ጉዳተኞች የአካል ድጋፍ እና የማህበራዊ ተሃድሶ አገልግሎት ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል።ይሄም ድጋፍ የተደረገላቸውን አካል ጉዳተኞች ቁጥር 511ሺህ 205 አድርሶታል። በዚሁ ዓመት ለብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት 14 ሚሊዮን 419 ሺህ 500 ብር ድጋፍ ተደርጓል። ይህም ድጋፍን 22 ሚሊዮን 60 ሺህ 750 ብር አድርሶታል።

ሌላው የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ በበጀት ዓመቱ የተከናወነው ተግባር 248 ለሚሆኑ አካል ጉዳተኞች ከቀረጥ እና ከታክስ ነፃ ተሽከርካሪ እንዲያስገቡ አገልግሎት መስጠት ተችሏል። ለአካል ጉዳተኞች ራሱን ችሎ ከሚደረግላቸው ልዩ ልዩ ድጋፎች በተጨማሪ ከሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር ተጠቃሚ የሆኑበት ሁኔታ እንዳለም ያወሳሉ ኃላፊው። ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ ሴቶች፣ ህፃናት፣ አረጋውያንና ሌሎች የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጠቂ የሆኑ ዜጎች ከተባበሩት መንግስታት ድርጀት (UNCIF) በተገኘ ድጋፍ በ‹‹Humanitarian Cash Transfer Programmer›› ተጠቃሚ ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞም አካል ጉዳተኞችም በዚህ ፕሮግራም እንደተጠቀሙም ያነሳሉ።

ከተለያዩ የሲቪል ማህበረሰብ እና ሌሎች አጋር ድርጅቶች እንዲሁም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ 1ቢሊዮን 349 ሚሊዮን 976 ሺህ 667 ብር ግምት ያላቸው የምግብ፣ አልባሳትና የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ድጋፍ የአካል ጉዳተኞችን ተካታችነት፣ ተሳታፊነትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ያረጋገጠ ነበር። በተጨማሪም በገጠርና በከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት መርሐ ግብሮች ተሳታፊ እንዲሆኑ፤ የቋሚ ቀጥታ ድጋፍ እንዲያገኙ ማስቻሉን ይጠቅሳሉ።

ኃላፊው እንደሚናገሩት፤ አካል ጉዳተኞች ከቁጥራቸው ስፋት እና ካለባቸው ጉዳት አንጻር ከሌሎች ጉዳት አልባ ከሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር ሲወዳደሩ ተጠቃሚነታቸው እጅግ ውሱን ነው። በመንግስት ተቋማት 2011/12 ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መረጃ በመንግስት ተቋም ከአንድ ሚሊዮን በላይ ከሚሆኑ ከመንግስት የሠራተኞች ውስጥ የአካል ጉዳተኞች ቁጥር ከ6ሺህ አይበልጡም። በመሆኑም በመንግስት ቅጥር ውስጥ ያለው የአካል ጉዳተኛ እጅግ አናሳ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

እንደሳቸው ገለጻ፤ በቅጥር ተጠቃሚ ያልሆኑት ሳይኖሩ ቀርተው አይደለም። ቁጥራቸው እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የተማሩና በመማር ላይ ያሉ አካል ጉዳተኞች አሉ። በቅጥር ላይ ሲኬድ ግን ችግሮች ይገጥሟቸዋል። በአሰሪዎች ዘንድ አካል ጉዳተኞችን ከመቅጠር ይልቅ ላለመቅጠር ምክንያቶች ይደራደራሉ። ይሄ ሥራ ለአንቺ (ለአንተ) አይሆንም፤ አካል ጉዳተኛ ስለሆንሽ (ስለሆንክ) ሥራውን በትክክል ልትሰሪው(ራው) አትችይም



የአካል ጉዳተኞች የአድቮኬሲና መብት ጥበቃ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሲሳይ ጥላሁን

(ልም) በማለት ሁሉንም መመዘኛ አሟልተው ሳለ በጉዳታቸው ብቻ የቅጥር ዕድሉን የሚነፈጉበት ጊዜ ብዙ ነው።

አቶ ሲሳይ እንደሚናገሩት፤ 568/2000 የወጣውን የሥራ ስምሪት አዋጅ በትክክል ይዞ ከመጓዝ አንፃር ተቋማት ላይ የግልፀኝነትና ቁርጠኝነት ችግር ጎልቶ ይስተዋላል። እንደሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ይሄ አዋጅ ወደ መሬት እንዲወርድና የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት በተገቢው መንገድ እንዲጎላ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እየተሰራ ይገኛል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ሌሎች ተቋማት ያሉ የሰው ሀብት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በአዋጁ ላይ በተደጋጋሚ ግንዛቤ እንዲጨብጡ የተደረገበት ሁኔታ አለ። ስለዚህም ተቋሙ እነዚህ ዓይነቱ ልክ ያልሆነ አመለካከት የወለደው አሠራር ላይ ለውጥ መምጣት እንዳለበት ያምናልና ለውጡን ለማምጣት ሰፊ ሥራ የሚሰራ ይሆናል።

የመንግስት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ 1263/2014 ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው፤እያንዳንዱ ተቋም የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በሚሰራቸው ሥራዎች በሙሉ አካቶ መሥራት እንዳለበት የሚደነግግ መሆኑን ያወሳሉ። እያንዳንዱ ተቋም በሚሰጣቸው አገልግሎቶች የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ ማጉላት አለበት ይላሉ። ለምሳሌ፡- በጤናው ዘርፍ የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ጤና ሚኒስቴር እስከ ታችኛው መዋቅር በስፋት እየሰራበት ያለ መሆኑን ያስታውሳሉ።

ተደራሽነትን በተመለከተ አካል ጉዳተኞች አገልግሎቶችን ፈልገው ሲሄዱ በትክክል ይጠቀሙበታል ወይ፤ ምቹና ተደራሽ ነው ወይ? የሚለውን ማረጋገጥም ያስፈልጋል ይላሉ። ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጀምሮ እስከ ታችኛው የጤና ተቋም ያሉ የጤና ባለሙያዎች ለአካል ጉዳተኛ ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ማጉላት እንደሚያስፈልግም ያብራራሉ።

ኃላፊው በትምህርቱ ዘርፍም የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት ምን እንደሚመስል አስመልክተው ሲናገሩ በትኩረት ታይቶ በስፋት መሰራት ያለበት እንደሆነ ይጠቁማሉ። በአጠቃላይ የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት የማረጋገጥ መብቱ በአዋጅ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተሰጠው ከመሆኑ አኳያ መስሪያ ቤታቸው በየዓመቱ በዕቅድ ውስጥ ተካትቶ ክትትል እየተደረገበት ያለ መሆኑን ይናገራሉ። በዚህ በኩል ትምህርት ሚኒስቴር ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ትኩረት ሰጥቶ እየሰራበት በመገኘቱ በእጅጉ የሚበረታታ መሆኑንም ይጠቅሳሉ።

ሌሎች ተቋማትም ይሄንኑ የትምህርቱን ዘርፍና በሌሎች መስኮች ያለውን የአካል ጉዳተኝነት ተጠቃሚነት አካተው መስራት እንደሚኖርባቸውም ያሳስባሉ። የአካል ጉዳተኞች በሕብረተሰብ ውስጥ አንድ የሕብረተሰብ ክፍል እንደመሆናቸው መጠን በተቋማቸው ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት አካል ጉዳተኞችን ያካተተና ተጠቃሚነታቸውን የሚያጎላ መሆን አለበትም ሲሉ ያስገነዝባሉ።

# ስፖርት





## የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ዳርት ቻምፒዮናን ለማዘጋጀት ጥረት እየተደረገ ነው

ዓለማየሁ ግዛው

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄደውን የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ዳርት ቻምፒዮና ለማዘጋጀት ጥረት እያደረገች መሆኑን የኢትዮጵያ ዳርት ፌዴሬሽን አስታውቋል። በዚህም ውድድር ኢትዮጵያን በመወከል በዓለም ዳርት ቻምፒዮና ሳይሳተፍ የቀረው ብሄራዊ ቡድን እንደሚሳተፍ ተገልጿል።

በአፍሪካ አህጉር ደረጃ የዳርት ካውንስል ባለመቋቋሙ የሀገራት ዳርት ቻምፒዮና ማካሄድ እንዳልተቻለ ይታወቃል። ባለፈው ዓመት የተደረገውን የካውንስል ምስረታ ተከትሎም ዘንድሮ የመጀመሪያ ጉባኤውን የሚያካሂድ ሲሆን፤ ኢትዮጵያም በተወካይዋ በኩል እንደምትሳተፍ ተረጋግጧል። በካውንስሉ አለመኖር ምክንያት በአህጉሪቷ የግል ክፍት ውድድሮች ብቻ ሲደረጉ ቆይተዋል። አሁን ባለው ሁኔታም በአህጉር አቀፍ ደረጃ የዳርት ቻምፒዮናን ለማካሄድ በጉባኤው ይወሰናል ተብሎ ይጠበቃል። ይካሄዳሉ ተብሎ ከሚጠበቁት የዳርት ውድድሮች ደግሞ በየዞኑ የሚደረጉትን ቻምፒዮናዎች ያካትታል። ከእነዚህም ውስጥ የምስራቅና መካከለኛ አፍሪካ ዳርት ቻምፒዮና አንዱ ሲሆን፤ ኢትዮጵያም የመጀመሪያውን ውድድር ለማዘጋጀት ጥረት እያደረገች መሆኑን ፌዴሬሽኑ አስታውቋል።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ በዴንማርክ አስተናግጅነት በተካሄደው የዓለም ዳርት ቻምፒዮና ለማሳተፍ ብሄራዊ ቡድኗን ስታዘጋጅ ብትቆይም ከቪዛ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በጊዜ ባለመጠናቀቃቸው ተሳትፎዋ መሰረዙ ይታወሳል። በወቅቱ ቡድኑ ከሁሉ ስፖርት በተደረገለት ድጋፍ በሆቴል ተሰባስቦ ዝግጅት ቢያደርግም የዴንማርክ ኤምባሲ ጊዜው አጭር በመሆኑና ከፍተኛ ወረፋ በመኖሩ ጉዳዩን መጨረስ እንደማይችል በማሳወቁ የኢትዮጵያ ተሳትፎ እውን ሊሆን አልቻለም። ሆኖም ለአዘጋጅነት ጥረት እየተደረገ ባለው የምስራቅ አፍሪካ ዳርት ቻምፒዮና እንዲሁም በሌሎች ውድድሮች ብሄራዊ ቡድኑ እንዲሳተፍ የማድረግ እድል ተፈጥሯል።

ለብሄራዊ ቡድኑ ዝግጅት የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ የትጥቅ ድጋፍ በማድረግ የተሻለ ዝግጅት ተደርጎ እንደነበረም ተጠቁሟል። ኢትዮጵያን በዓለም ዳርት ቻምፒዮና ለመወከል በ2015 ዓም ከተካሄደው የኢትዮጵያ ዳርት ቻምፒዮና የተመረጡ አራት ወንድና ሶስት ሴቶች በድምሩ 7 ስፖርተኞች ዝግጅታቸውን ሲያደርጉም ቆይተዋል። የኢትዮጵያ ዳርት ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ቢልልኝ መቆያ ብሄራዊ ቡድኑ በገጠመው ችግር ምክንያት በዓለም ቻምፒዮናው ባይሳተፍም የምስራቅ አፍሪካ ዳርት ቻምፒዮናን በማዘጋጀት እንዲወዳደር ጥረት እንደሚደረግ ገልጸዋል። በዚህም የስፖርተኞቹ ሞራል እንደይነካ በቀጣይ በሚደረጉት ውድድሮች እንዲሳተፉም እድል ተሰጥቷል። በስፖርት ዓለም የቪዛ ጉዳይ የሚያጋጥም በመሆኑ ተስፋ መቁረጥ እንደማያስፈልግና ፌዴሬሽኑ በዓለምና አፍሪካ ውድድሮች እንዲሳተፍ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርም ተናግረዋል።

ውድድሩን ለማዘጋጀት ዩጋንዳ ከሚገኝ የግል ውድድሮች አዘጋጅ ጋር ግንኙነት ከተጀመረ መቆየቱን የጠቆሙት አቶ ቢልልኝ፤ የዴንማርኩ ተሳትፎ ባለመሳካቱ ለስፖርተኞቹ እድል ለመስጠት ለነዚህ አዘጋጆች ጥያቄ ቀርቦላቸው ደብዳቤ እንዲላክላቸው መጠየቃቸውንም ጠቅሰዋል። የውድድሩ አዘጋጆች የግብዣ ደብዳቤ ከተላከላቸው በኋላ በጥቅምት ወር መጨረሻ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ከኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ ከባለ ድርሻ አካላትና ከፌዴሬሽኑ ስራ አስፈጻሚ ጋር ተነጋግሮ በቅርብ ጊዜ የአፍሪካ ውድድሮች በተለይ የምስራቅና መካከለኛ አፍሪካ ቻምፒዮና ይዘጋጃል። የአፍሪካ ዳርት ቻምፒዮናም ለመጀመሪያ ጊዜ በግብጽ አስተናጋጅነት ሊካሄድ እንደሚችል የጠቀሱት ፕሬዚዳንቱ ኢትዮጵያ ተሳትፎዋን እንደምታደርግ ጠቁመዋል።

የዳርት ስፖርት የቤት ውስጥ ውድድር በመሆኑ ምቹ የሆነ ሆቴል ተመርጦ ለዝግጅቱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በማሟላት ውድድሩ የሚዘጋጅም ይሆናል። የአፍሪካ ዳርት ካውንስል ባለፈው ዓመት በመቋቋሙ እስከ አሁን ውድድሮች እንዳልተደረጉና የዘንድሮ ጉባኤ ከተደረገና ከተጠናከረ በኋላ በአፍሪካ ደረጃ ውድድር እንደሚካሄድ አቶ ቢልልኝ ይገልጻሉ። የግል ክፍት ውድድሮች በየሀገሩ የሚካሄዱ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን ተወዳዳሪዎች በዩጋንዳና ኬንያ በተደረጉ የግል ውድድሮች መካፈል ችለዋል። ለዚህም ፌዴሬሽኑ ድጋፍ ያደረገ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የምታደርገው ተሳትፎ ባይሳካም የምስራቅ አፍሪካን ውድድር ለማዘጋጀት ፌዴሬሽኑ እየሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የዳርት ስፖርት በሁሉም ክልሎች የሚከወን ቢሆንም ከመንግስትና ከባለ ድርሻ አካላት የሚሰጠው ትኩረት ዝቅተኛና እንደ ስፖርት የሚመለከቱት አካላት ጥቂት በመሆናቸውም ለስፖርቱ ዕድገት እንቅፋት ሆኗል። ዳርት የአእምሮ ብልጽግናን፣ እርግጠኝነትንና ትኩረትን የሚያሳድግ ስፖርት በመሆኑ ፌዴሬሽኑ ስፖርቱ እንዲያድግ ትኩረት በመስጠት አጠናክሮ ይሰራል።


### የሂሳብ ማጣራት ስራ ማስታወቂያ

ኤ ኤም ኤስ ኤም ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የተባለ ድርጅት በመስከረም 10/2016 አባላት ባደረጉት ስብሰባና በመስከረም 10/20 በሰነዶች ማረጋገጫ በፀደቀው መሰረት ማህበሩ እንዲፈርስ መወሰናቸውን መሰረት በማድረግ የሂሳብ ማጣራት ስራውን ሰርተናል፡፡ ስለዚህ በንግድ ህግ ቁ.18 መሰረት ከድርጅቱ ላይ ገንዘብ ወይም ንብረት አለኝ የሚል አካል ካለ መረጃውን ይዞ በአጣሪው ቢሮ አድራሻ አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 014 ሴካ የንግድ ማዕከል 6ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 119 በስራ ሰዓት ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት እስከ አስራ አንድ ሰዓት ባለው ጊዜ መረጃውን ይዞ በ90 ቀናት ውስጥ ማመልከት ይችላል፡፡

**አህመድ ያሲን የተፈቀደለት የሒሳብ አዋቂ**

### የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የንግድ ምልክት ባለቤት ስም፡- አል-ሀሰን ፉድ ኢንዱስትሪስ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር/ Al-Hassan Food Industries P.L.C
አድራሻ፡- ወረዳ 03፡ የቤት ቁ 2482, ቦሌ, አዲስ አበባ
2. የማመልከቻ ቁጥር፡ LTM/3802/2016
3. የጥበቃ ጊዜው፡ ከ 12/07/2015 እስከ 12/07/2022
4. የንግድ ምልክት፡




5. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በ ዓ.ም በ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው፡፡
6. ይህ የንግድ ምልክት የታደሰ በመሆኑም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጭ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**
ADDIS ZEMEN VOl-LXXXIII No-022 22/1/2016 (3/10/2023)

### ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት

በአመልካች ሸውሞሎ ሞሳ ረጃቶ እና በተጠሪ አቶ አቤነዘር አባተ ኢጃታ መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክስ ጉዳይ ተከሳሽ አቤነዘር አባተ ኢጃታ በቀረበበት ክስ የፍ/ቤቱ መጥሪያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲጠራ የታዘዘ ሲሆን ተፈላጊው ጥቅምት12 ቀን2016ዓ.ም ለተያዘው ቀጠሮ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በስልጤ ዞን የወራቤ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲቀርብ ባይቀርቡ ግን ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን በመግለጽ በትዕዛዙ መሰረት እንዲፈጸም የወራቤ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አዟል፡፡

**በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት በስልጤ ዞን የወራቤ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር አዲስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0004751973 ክፍሌ ደምስስ ደሱ የተመዘገብኩበት ቦሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ውስጥ ከቁጥር 0001 እስከ 0039 የተሰራበት እና ከቁጥር 0040 እስከ 00250 ያልተሰራበት እንዲሁም የተርን ኦቨር ታክስ (ቲኦቲ) የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ውስጥ ከቁጥር 00201 እስከ 00210 የተሰራበት እና ከቁጥር 00211 እስከ 0250 ያልተሰራበት የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ቦሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ክፍሌ ደምስስ ደሱ**

### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 2616/ሀ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0006755720 ዳንኤል ተከተል አባተ የተመዘገብኩበት ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ውስጥ ከቁጥር 0401 እስከ 0450 ያልተሰራበት የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ዳንኤል ተከተል አባተ**